የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION
1993

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# የፌዴራል

# መንግሥት የመንገድ መሠረተ ልማት

# ፕሮጀክቶች የውል አስተዳደር ጥናት


**አጥኚ ባለሙያዎች፡ -**

- **ደምሴ ስንሻው፡ - ቡድን መሪ**
- **እፀገነት ደባስ፡ - ቡድን አባል**
- **ቤዛ አማኑኤል፡ - ቡድን አባል**



ሰኔ/2017 ዓ.ም    አዲስ አበባ

ማውጫ ገጽ

**ርዕስ**


1. መግቢያ.....1
2. የጥናቱ ዋና ዓላማ.....2
2.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ.....2
2.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች.....2
3. የጥናቱ ግብ.....2
4. የጥናቱ መረጃ ምንጮችና የተገኙ መረጃዎች፣.....2
4.1 የጥናቱ መረጃ ምንጮች.....2
4.1.1 የተለያዩ ሰነዶች ፍተሻ.....6
4.1.2 ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ.....6
4.1.3 የመስክ ምልከታ በማድረግ.....7
4.2 በጥናቱ የተገኙ መረጃዎች፣.....7
4.2.1 የግዥ ጨረታ ሂደት.....7
4.3 የውል አስተዳደር.....15
4.3.1 ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ.....20
4.3.2 የኦዲት ቁጥጥር.....23
4.3.3 የመስክ ምልከታ.....24
5. የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች በርዕስ ጉዳይ.....34
5.1 የግዥ ጨረታ በሚመለከት.....35
5.2 የውል አስተዳደር በሚመለከት.....35
5.3 ቃለ-መጠይቅ በሚመለከት.....37
5.3.1 የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር፡-.....37
5.3.2 ከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር፡-.....37
5.3.3 የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን፡-.....38
5.4 ኦዲትን በሚመለከት.....38
5.4.1 የተቋሙ የውስጥ ኦዲት፡-.....38
5.4.2 የፌደራል ዋናው ኦዲተር፡-.....38
5.5 የመስክ ምልከታ.....39

6. የጥናቱ ምክረ-ሐሳብ፣ ........................................ 40
6.1 የፌደራል መንገዶች አስተዳደር፡- ........................................ 40
6.2 በተጨማሪ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ........................................ 43
መሠረት በመንገድ ፕሮጀክቶች፡- ........................................ 43
7. የጥናቱ ምክረ-ሐሳብ ክትትልና ድጋፍ ስልቶች፣ ........................................ 44
8. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች፣ ........................................ 46
8.1 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ........................................ 46
8.2 በጥናቱ ወቅት የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች፣ ........................................ 46
ማጠቃለያ ........................................ 47
አባሪዎች ........................................ 48
አባሪ 1 ........................................ 48
አባሪ 2 ........................................ 51
ዋቢ ማጣቀሻዎች ........................................ 55

## 1. መግቢያ

የመንገድ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ተግባራዊ ለማድረግ በዘርፉ የሚስተዋለውን ተግዳሮት ለመፍታት ተከታታይነት ያለው ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ የመንገድ መሠረተ ልማት በአግባቡ ከተስፋፋ የግብዓትና የምርት ሸቀጦችን ዝውውር በማቀላጠፍ ኢኮኖሚውን ለማሳደግ ጉልህ ሚና ይጫወታል፡፡

የመንገድ መሠረተ ልማት ግዥና ውል አስተዳደር ሂደት ውስጥ የሚፈፀም ሙስናና ብልሹ አሰራር እንዲቀንስ፣ የግዥ ውልን በግልጽነት መፈፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ፋይዳቸው እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ በተቋማት የሙስናና ብልሹ አሠራር እንዲከሰት ምክንያት ከሚሆኑት መካከል ግልፅነት የጎደላቸው አሠራሮች (ግዥዎች፣ ውሎች፣ ወዘተ.)፣ ያልተገደበ ሥልጣን፣ ጠንካራ ያልሆነ የቁጥጥር ሥርዓት፣ የሠራተኞች የሥነምግባር ብልሽት፣ ወዘተ. ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ሙስናን ለመፈፀም ፍላጎት ያላቸውን አካላት ስለሚያማልል የግዥ ውሳኔ ሰጪዎችና የግዥ ሠራተኞች በአንድ በኩል፤ አቅራቢ የሥራ ተቋራጮች እና አማካሪዎች በሌላ በኩል የጥቅም ግንኙነት በመፍጠር በቀላሉ የማይገመት የመንግሥት ገንዘብ እንደሚባክን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የጥቅም ትስስር ምክንያት የግዥ አሰራሮች እንዲጣሱ በማድረግ የሥራዎች ጥራት እንዲቀንስ፣ ከወጣባቸው ወጪ ጋር የሚመጣጠን አገልግሎት የማይሰጡ በመሆናቸው ተቋማትን ለተጨማሪ ወጪ ይዳርጋሉ፣ ሥራዎች በወቅቱ ካልተከናወኑ የመንግስት ተቋማት ዕቅድ አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳርፋሉ፡፡

በመሆኑም የመንገድ ፕሮጀክቶች ውል አስተዳደር ግልጽ መሆን ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እንደ ቅድመ ሁኔታ ይቆጠራል፡፡ የቁጥጥር ተቋማት እና አጠቃላይ ህዝቡ በመንግስት ግዥ አፈፃፀም ሂደትና ውል አስተዳደር ላይ የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮችን ከመከላከል አንፃር የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ምቹ ሁኔታ መፍጠር በመንግሥት የሚፈፀም የመንገድ ፕሮጀክቶች ግዥና የውል አስተዳደር አሠራርን በማጠናከር ረገድ ጥናቱ የጎላ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

# 2. የጥናቱ ዋና ዓላማ

## 2.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ

በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የውል አስተዳደርና አፈፃፀም ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመፈተሽ ክፍተቶችን መፍታት የሚያስችል ምክረ-ሃሳብ ለማቅረብ ነው፡፡

## 2.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

- በኢትዮጵያ መንገድ አስተዳደር የግዥ ሂደትና የውል አስተዳደር ላይ የሚታዩ የአሠራር ችግሮችን ለመፈተሽ፣
- ለግልፅነት መጓደል ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ አሠራሮችን ለመለየት፣
- ትክክለኛ አሠራር አለመኖር ሊያስከትል የሚችለውን አሉታዊ ውጤት ለማመላከት፣
- በግዥ ጨረታ ሂደትና በውል አስተዳደር ትክክለኛ አሠራር ለማስፈን የሚያግዙ ምክረ-ሃሳቦችን ማመላከት ነው፡፡

# 3. የጥናቱ ግብ

በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ ተብሎ በተለዩ የግዥ ጨረታ ሂደትና የውል አስተዳደር ዙሪያ የሚደረገውን እንቅስቃሴ በማጥናት ሙስናንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ምክረ-ሀሳብ ማቅረብ፡፡

# 4. የጥናቱ መረጃ ምንጮችና የተገኙ መረጃዎች፣

## 4.1 የጥናቱ መረጃ ምንጮች

ጥናቱን ለማካሄድ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ስራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ **የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎች** በተዘጋጀ የመረጃ ማሰባሰቢያ ቃለ-መጠይቅ መሠረት በማድረግ **ከኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር፣ ከከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር እና ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን** የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች፣ የመንገድ ፕሮጀክት ሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች፣ የመንገድ ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ የአካባቢ ነዋሪዎችን እና የመስተዳደር አካላትን ትኩረት በማድረግ መረጃው ተሰብስቧል፡፡

የሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች ቀደም ሲል በተቋሙ ለመንገድ ሥራዎች የተለያዩ ውል የተፈፀመባቸው ሰነዶች፣ ከኦዲትና ዓመታዊ አፈፃፀም ሪፖርቶች፣ ከአዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ማንዋሎችን በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

| ኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር በ2017 በጀት ዓመት በጥናቱ ለክለሳ የተመረጡ ፕሮጀክቶች ዝርዝር | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ/ቁ | ፕሮጀክቱ ሥም | የፕሮጀክቱ ጠቅላላ ኪ.ሜ. | የሚሠራበት ቦታ | የመጀመሪያ የውል ጊዜ | የፕሮጀክቱ ውል የሚጠናቀቅበት ጊዜ | የፕሮጀክቱ ውል ማሻሻያ ጊዜ | የተያዘ በጀት | ተጨማሪ በጀት | እስከ 2017 ሰኔ ወር መጨረሻ የወጣ ወጪ /Expenditure To Date አድቫንስን ጨምሮ /በቢሊ/ሚሊ.ብር | እስከ ሰኔ 2017 የተሰራ የፊዚካል ሥራ |
| 1 | ተርጫ - ወልደሀና - ወረቦ (ሎት.1) | 83 | ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | መጋቢት 2012 | ጳጉሜ 2016 | ጳጉሜ 2016 በግምገማ ላይ ያለ | 2,450 | 2,450 | 1,264 (52%) | 25 (30%) |
| 2 | ጫንቃ-ጊዳሚ | 97 | ኦሮሚያ | ጥቅምት 2014 | ጥቅምት 2018 | ጥቅምት 2018 | 3,207 | 3,207 | 969 (30%) | 13 (13%) |
| 3 | ነቀምት-ሶጌ-ካማሽ-ኮንቾ (ሎት 1 ነቀምት-ኪ.ሜ105) | 105 | ኦሮሚያ | ሰኔ 2016 | ሰኔ 2019 | ሰኔ 2019 | 9,371 | 9,371 | 846 (9%) | 1.5(1.4%) |
| 4 | ሱፔ-ዳራሙ-ላሎቅሌ | 91 | ኦሮሚያ | ጥቅምት 2015 | ጥቅምት 2019 | ጥቅምት 2019 | 2,916 | 2,916 | 1,016 (35%) | 13(14%) |
| 5 | ጋሸና- ቢልቢላ | 105 | አማራ | የካቲት 2006 | ነሃሴ 2009 | ጥቅምት 2014 | 4,705 | 4,705 | 1,662 (35%) | 91(87%) |
| 6 | ዱርቤቴ-ቁንዝላ-ገላጎ-መተማ (ሎት 3፡ ኪ.ሜ170-መተማ ገለጎ-ገንደ ዉሃ) | 125 | አማራ | ሀምሌ 2013 | ጥር 2017 | ሀምሌ 2017 | 2,719 | 2,719 | 2,090 (77%) | 37(30%) |
| 7 | ዋርዴር -ቀብሪደሀር | 139 | ሶማሌ | ሰኔ 2011 | ሰኔ 2015 | መጋቢት 2017 | 1,814 | 1,932 | 1,119 (58%) | 95.82(69%) |
| 8 | አሰብ ኮሪደር (ሜለዱን መገንጠያ - ማንዳ - ቡሬ) | 70 | አፋር | ጥቅምት 2013 | ሚያዚያ 2016 | ጥቅምት 2017 | 2,086 | 1,591 | 1,227 (77%) | 47.36 (67%) |
| 9 | ሻሸመኔ-አላባ | 67 | ኦሮሚያ እና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | የካቲት 2013 | የካቲት 2016 | ሀምሌ 2017 | 2,900 | 2,900 | 2,008 (69%) | 21.67(33%) |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | ዲላ-ቡሌ-ሀረዋጮ-ሻኪሶ (ሎት 1፡ ዲላ-ቡሌ-ሀረዋጮ) | 68.87 | ደቡብ ኢትዮጵያ እና ኦሮሚያ | ሚያዚያ 2015 | ሚያዚያ 2019 | ሚያዚያ 2019 | 2,456 | 2,456 | 379 (15%) | 6.10(9%) |
| 11 | ቱርሚ-ወይጦ | 120 | ደቡብ ኢትዮጵያ | ግንቦት 2013 | ግንቦት 2017 | ግንቦት 2017 | 2,843 | 2,848 | 1,513 (53%) | 30.95(26%) |
| 12 | ሮቤ-ጎሮ-ሶፉመር-ጊኒር መገንጠያ | 123 | ኦሮሚያ | መጋቢት 2015 | መጋቢት 2018 | መጋቢት 2018 | 8,798 | 8,798 | - | 59(48%) |
| 13 | መልካሳ--ሶደሬ-ኑራሄራ-መተሀራ መገንጠያ | 94 | ኦሮሚያ | ጥር 2010 | ህዳር 2013 | ህዳር 2014 | 1,203 | 1,441 | 1,214 (84%) | 50(53%) |
| 14 | ገንደሸዋ-ኤጄሬ-ጉንዶመስቀል-ወለቃ- ቀይማብራት( ሎት 1፡ ገንደሸዋ-ኤጄሬ- ጉንዶመስቀል) | 88 | ኦሮሚያ | ጥቅምት 2015 | ጥቅምት 2018 | ጥቅምት 2018 | 5,337 | 5,337 | - | 0 |
| 15 | አርሲ ነገሌ-ሀዋሳ | 52.2 | ኦሮሚያ | የካቲት 2010 | ጳጉሜ 2013 | ጥቅምት 2017 | 4,857 | 5,351 | 3,149 (59%) | 34 (65%) ተቋርጦ የቆየ እና 2018 በጀት የተያዘለት |
| 16 | አጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ -ጌጃ-ሌራ | 97.011 | ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጥር 2009 | ግንቦት 2012 | ጥር 2018 | 1,165 | 5,155 | 2.536(49%) | 32.37(33%) |
| 17 | ወራቤ-ቦጀበር | 41.35 | ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ግንቦት 2008 | ጥቅምት 2011 | መስከረም 2018 | 458 | 2,777 | 1,301(47%) | 34.86(85%) |
| 18 | ጨበራ-ጩርጩራ-ጉዱሙ (ሎት 1፡) | 118 | ደቡብ ምዕራብ | ሰኔ 2013 | ጥር 2014 | ሰኔ 2016 | 2,617 | 2,845 | 535 (19%) | 17(14%) |
| 19 | ቱሉ ቦሎ-ኬላ | 79.9 | ኦሮሚያ እና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጥቅምት- 2009 | ሚያዚያ 2013 | ጥቅምት 2017 | 1,309 | 1,739 | 211 | 97.41(97%) (የመያዣ ክፍያ) |
| 20 | ኤፌሶን (አጣዬ) -መሀል ሜዳ | 60 | አማራ | ሚያዝያ 2007 | ሚያዝያ 2009 | መስከረም 2014 | 1,353 | 1,353 | 1,233 | 60 (የማጠናቀቂያ ስራ) |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 21 | ጣርማበር - መለያያ-ሰፌድሜዳ ስተር | 119 | አማራ | ህዳር 2011 | ታህሳስ 2014 | የካቲት 2015 | | | |

**ኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር በ2017 በጀት ዓመት በጥናቱ ከተከለሱት መካከል ተጨማሪ ጊዜና በጀት የጠየቁ ፕሮጀክቶች**

| ተ/ቁ | ፕሮጀክቱ ሥም | የፕሮጀክቱ ጠቅላላ ኪ.ሜ. | የመጀመሪያ የውል ጊዜ | ውል የሚጠናቀቅበት ጊዜ | የውል ማሻሻያ ጊዜ | የተያዘ በጀት | ተጨማሪ በጀት | እስከ 2017 ሰኔ ወር መጨረሻ የወጣ ወጪ /Expenditure To Date አድቫንስን ጨምሮ /በቢሊ/ሚሊ.-ብር | እስከ ሰኔ 2017 የተሰራ የፊዚካል ሥራ አፈፃፀም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ዋርጄር -ቀብሪደሀር | 139 | ሰኔ 2011 | ሰኔ 2015 | መጋቢት 2017 | 1,814 | 1,932 | 1,119 (58%) | 95.82(69%) |
| 2 | ቱርሚ-ወይጦ | 120 | ግንቦት2 013 | ግንቦት201 7 | ግንቦት 2017 | 2,843 | 2,848 | 1,513 (53%) | 30.95(26%) |
| 3 | መልካሳ--ሶደሬ-ትራሄራ-መተሀራ-መገንጠያ | 94 | ጥር 2010 | ህዳር 2013 | ህዳር 2014 | 1,203 | 1,441 | 1,214 (84%) | 50 (53%) |
| 4 | አርሲ ነገሌ-ሀዋሳ | 52.2 | የካቲት 2010 | ጳጉሜ 2013 | ጥቅምት 2017 | 4,857 | 5,351 | 3,149 (59%) | 34 (65%) ተቋርጦ የቆየ እና 2018 በጀት |
| 5 | አጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ -ጌጇ-ሴራ | 97.011 | ጥር 2009 | ግንቦት 2012 | ጥር 2018 | 1,165 | 5,155 | 2.536 (49%) | 32.37(33%) |
| 6 | ወራቤ-ቦጀበር | 41.35 | ግንቦት 2008 | ጥቅምት 2011 | መስከረም 2018 | 458 | 2,777 | 1,301(47%) | 34.86(85%) |
| 7 | ጨበራ-ጩርጩራ-ጉዱሙ (ሎት 1፡) | 118 | ሰኔ 2013 | ጥር 2014 | ሰኔ 2016 | 2,617 | 2,845 | 535 (19%) | 17(14%) |
| 8 | ቱሉ ቦሎ-ኬላ | 79.9 | ጥቅምት-2009 | ሚያዚያ 2013 | ጥቅምት 2017 | 1,309 | 1,739 | 211 | 97.41(97%) (የመያዣ ክፍያ) |
| 9 | ጣርማበር - መለያያ-ሰፌድሜዳ ስተር 1 መለያያ ስተር 2 ሞላሌ-ወገሬ | 119 | ህዳር 2011 | ታህሳስ 2014 | የካቲት 2015 | 1,906 | 2,142 | 432 | 21(17.6%) |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ድምር | 860.46<br>1 | | | | 18,172 | 26,230 | | |

የፌደራል መንግስት በ2017 በጀት ዓመት በሀገሪቱ **167** የሚሆኑ የመንገድ ስራ ፕሮጅክቶች በብር **95.97** ቢሊዮን ለመሥራ እቅድ የተያዘ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ በዚህ ጥናት 21 የመንገድ ስራ ፕሮጅክቶች **በብር 74.033 ቢሊዮን** በሆነ መዋለ ንዋይ በተለያዩ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመንገድ ፕሮጀክቶች መነሻ በማድረግ የሰነድ ክለሳ አድርጓል፡፡

በዚህ መሰረት ከእነዚህ 21 ፕሮጀክቶች ውስጥ 13ቱ ወይም 61.9% የሚሆኑት የመንገድ ፕሮጀክቶች ተጨማሪ ጊዜ (ከ1 ዓመት እስከ 7 ዓመት እና በላይ የተጠየቀባቸው ናቸው፡፡

የ9 የመንገድ ስራ ፕሮጀክቶች በንጽጽር ሲታዩ በመጀመሪያው እቅድ ጠቅላላ ዋጋቸው **ብር 18.172 ቢሊዮን** ሲሆን በተከለሰው እቅድ ብር **26.23 ቢሊዮን** በላይ ደርሷል፡፡ በዚህ ምክንያት **በልዩነት ከብር 8.06 ቢሊዮን** በላይ ተጨማሪ ወጪ የተደረገ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

እነዚህ 21 የመንገድ ስራ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው በጀትና ጊዜ ያልተጠናቀቁ፣ ተጨማሪ ወጪን የጠየቁ፣ ፕሮጀክቶችን በጊዜው ለማጠናቀቅ የክትትልና የቁጥጥር ክፍተት እንዳለ መረጃዎች የሚያሳዩ ሲሆን ይህ ጥናት በ21ቱ የመንገድ ስራ ፕሮጀክቶቹ ላይ የሚስተዋሉትን የአሰራር ክፍተት መነሻ በማድረግ በናሙና በተመረጡ **የአጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሌራ እና የወራቤ-ቦጀበር** የመንገድ ስራ ፕሮጀክቶች ላይ በማተኮር የተካሄደ ነው፡፡

### 4.1.1 የተለያዩ ሰነዶች ፍተሻ

ለጥናቱ አገልግሎት የተለያዩ ሰነዶችን በመጠቀም መረጃዎች የተሰበሰበ ሲሆን ከነዚህም መካከል በመሠረተ ልማት ፕሮጀክቱ ዙሪያ የግዥ ጨረታ ሂደቶችን የሚያሳዩ እና የውል አስተዳደር ሰነዶች፣ የመ/ቤቱ ሪፖርቶች፣ የውስጥና የውጭ ኦዲት ሪፖርቶች፣ የካሳ ክፍያ የተፈፀመባቸው፣ የአዋጭነት ጥናት እንዲሁም አዋጆችና ደንቦች በመረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

### 4.1.2 ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ

የቃለ መጠይቅ አንዱ የጥናት መረጃ መሰብሰቢያ ስልት በመሆኑ ለጥናቱ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የሚታመንባቸው የተጠኚ መ/ቤቱ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች፣ የአካባቢ ነዋሪዎች እና የመስተዳደር አካላት በተናጠልና በቡድን ፊት ለፊት ውይይት ተከናውኗል፡፡

### 4.1.3 የመስክ ምልከታ በማድረግ

በፌደራል የመንገድ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች እና በናሙና በተመረጡ **አጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ-ጊጃ-ሴራ እና ወራቤ-ቦጆበር ፕሮጀክቶች** ላይ በአካል ምልከታ በማድረግ፣ አጠቃላይ የፕሮጀክቶች አፈፃፀም ሙስናና ብልሹ አሠራር መኖሩን በተመለከተ ጠቃሚ መረጃዎችን ለማግኘት በመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ተግባራዊ ሆኗል፡፡

## 4.2 በጥናቱ የተገኙ መረጃዎች፣

የዚህ የትግበራ ጥናት አቀራረብ የግዥ ጨረታ አፈፃፀም ሂደትና የውል አስተዳደር ማሳያዎችን፣ የውጭ እና የውስጥ የኦዲት ሪፖርት ግኝቶችን፣ ወዘተ. በመተንተን ሥራ ላይ ውሏል። ከቃለ-መጠይቅና ከተለያዩ ምንጮች (ሰነዶችና እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች) የተሰበሰቡ መረጃዎችን በቅይጥ ዘዴ (Mixed Approach) በመጠቀም ዓይነታዊ (Qualitative) እና መጠናዊ (Quantitative) በመተንተን በሰፊው ተቀባይነት ያለውን የጭብጥ (ተግባራዊ) ትንተና (thematic analysis) ተጠቅሟል።

### 4.2.1 የግዥ ጨረታ ሂደት

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ለማቋቋም በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 247/2003 መሰረት የፌዴራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የመንገዶችን ዲዛይን የሚሠሩ ወይም የቁጥጥርና ተዛማጅ አገልግሎቶችን የሚሰጡ አማካሪዎችን እንዲሁም በመንገድ ሥራዎች የሚሰማሩ ሥራ ተቋራጮች የሚመረጡበትን ዘዴዎች ይወስናል፤ በሚለው ተቋሙ የመንገድ ፕሮጀክት የግዥ ጨረታ እቅድ እንደሚያዘጋጁ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የፌዴራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ለማስፈፀም ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌደራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሠረት መ/ቤቱ በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈፅማቸው ግዥዎች በድረ-ገጽ የሚያወጣውን ወቅታዊ የዋጋ ዝርዝርና በግዥ ስራ ክፍሉ የሚካሄድ የገበያ ጥናት በመጠቀም ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን ማመን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ተቋሙ የገበያ ጥናት በማድረግ ከዝቅተኛ አቅራቢው ግዥ እንደሚፈፀም የተገኙ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በተቋሙ የመንገድ የጨረታ ግዥ የሚፈጽሙት በግዥ እቅድ መሰረት በመለየት እንደሆነ ቢገለፅም የጨረታ ግዥ አፈፃፀማቸው እንደሚያሳየው የግዥ ሥርዓትን ተከትሎ ከመፈጸም አንፃር መጀመሪያ የተከናወነው የግዥ ጨረታ በእቅዱ መሠረት ሥራው ሳይጠናቀቅ ወይም ሳይከናወን **ለሁለተኛ እና ሦስተኛ** ጊዜ የመንገድ የግዥ ጨረታ የሚካሄድ ስለመሆኑ የተገኙ የሰነድ ማስረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ **ለማሳያ** ለዚህ ጥናት በናሙናነት የተመረጡት **አጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሴራ ሁለት ጊዜ፤ ወራቤ-ቦጆበር የመንገድ ፕሮጀክት ደግሞ ሦስት ጊዜ** የግዥ ጨረታ ስለመካሄዱ መረጃዎች የሚያሳዩ ሲሆን ዝርዝሩ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 1. የአጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሴራ የመንገድ ፕሮጀክት፡-

ይህ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት በ**ማዕከላዊ ኢትዮጵያ** ክልል ውስጥ የሚከናወን **51.82 ኪ.ሜ ጉራጌ ዞን፣ 14.78 ኪ.ሜ ሀድያ ዞን** እና **1.723 ኪ.ሜ ስልጤ ዞን** ውስጥ የሚገኝና አጠቃላይ **97.011 ኪ.ሜ** የሚሸፍን መሆኑን ከተሰባሰበው መረጃ መረዳት ተችሏል፡፡ የመጀመሪያውንና የሁለተኛውን የግዥ ጨረታ ሂደት ዝርዝር የመመዘኛ መስፈርቶችን ያካተተ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

የፕሮጀክቱ የመጀመሪያው በግልጽ የጨረታ አይነት ዘዴ የተካሄደ ሲሆን የግዥ ጨረታ ማስታወቂያ **የካቲት 13/2009 ዓ.ም** በቁጥር W/44/ICB/OC/GOE/2009 EFY እንደወጣና 22 ተጫራቾች የጨረታውን ሰነድ ገዝተው 6 ሞልተው እንደመለሱ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ **ሚያዝያ 28/2009 ዓ.ም** ጨረታው ተከፍቶ 4 ተጫራቾች ለፋይናንሽያል ግምገማ አልፈው ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው **"ሻንዶግ ሃይዌይ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን"** አሸናፊ ሆኗል፡፡ በሚከተለው ሠንጠረዥ የሥራ ተቋራጮች ውጤት ተመላክቷል፡፡

**የአጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሴራ የመጀመሪያ የተቋራጮች ጨረታ ግዥ ሠንጠረዥ 1፡-**

| ተ.ቁ | የሥራ ተቋራጭ ስም | ቴክኒካል/% | ፋይናንሽያል ብር |
|---|---|---|---|
| 1. | ሱር ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ | የብቃት መስፈርቱን ያሟላል | 1,621,800,000.00 |
| 2. | ሲጂሲ ኦቨርሲ ኮንስትራክሽን ግሩፕ | የብቃት መስፈርቱን ያሟላል | 1,495,132,859.57 |
| 3. | ቻይና ኮሙኒኬሽን ኮንትራክሽን ኩባንያ ሊሚትድ | የብቃት መስፈርቱን ያሟላል | 1,492,466,537.50 |
| **4.** | **ሻንዶንግ ሀይዌይ ኮንስትራክሽን ግሩፕ ኩባንያ ሊሚትድ** | **የብቃት መስፈርቱን ያሟላል** | **1,165,299,596.00** |
| 5. | የቻይና ሪልዌይ ሰቨንዝ ግሩፕ ኩባንያ ሊሚትድ | በቴክኒክ ግምገማ ወቅት ብቁ አይደለም | የፋይናንሺያል ጨረታ ሰነድ አልተከፈተም |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 6. | የቻይና ስቴት ኮንስትራክሽን ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ሊሚትድ | በቴክኒክ ግምገማ ወቅት ብቁ አይደለም | የፋይናንሺያል ጨረታ ሰነድ አልተከፈተም |

ለመጀመሪያው አማካሪ በቁጥር S/73/NCB/RP/GOE/2009/EFY **ጥር 25/2009 ዓ.ም** በወጣው ጨረታ 6 ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሰነድ ሲገዙ 5 ተወዳዳሪዎች ሞልተው አስገብተዋል፡፡ 5ቱም ለፋይናንሻል ውድድር ያለፉ ሲሆን **ኋይትናይት ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኮንሰልታንት ኃ/የተ/የግ/ማ ብር 20,670,100.00** (ሃያ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰባ ሺህ አንድ መቶ) ዝቅተኛ ዋጋ በማቅረቡ አሸናፊ ሆኗል፡፡ በሚከተለው ሠንጠረዥ የአማካሪዎች ውጤት ያመላክታል፡፡

**የአጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሴራ የአማካሪ የመጀመሪያ ግዥ ጨረታ ሠንጠረዥ 2፡-**

| ተ.ቁ | የአማካሪ መሐንዲሶች ስም | ቴክኒካል/% | ፋይናሽያል ብር | ጠቅላላ ነጥብ ከ100 | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ኤም ኤች ኢንጂነሪንግ አማካሪ መሐንዲሶች እና አርክቴክቶች ኃ/የተ/የግ/ማ | 64.96 | 51,433,584.40 | 72.19 | |
| 2. | ይዲዲያ ምህንድስና አማካሪዎች ኃ/የተ/የግ/ማ | 71.04 | 35,231,692.79 | 81.77 | |
| **3.** | **ኋይትናይት ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት አማካሪዎች ኃ/የተ/የግ/ማ** | **65.36** | **20,670,100.00** | **84.33** | **ውል የተሰጠው አሸናፊ ድርጅት** |
| 4. | **ልደት አማካሪ መሐንዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማ** | 64.96 | 19,695,377.25 | 84.96 | በነጠላ የጨረታ ሂደት ከፍተኛ ውጤት ቢያመጣም በተመሳሳይ ወቅት በወጡ ጨረታዎች የጨረታ ሰነድ ላይ በሚቀመጥ መስፈርት መሰረት ተጫራቹ የሌላ ጨረታ ኮንትራት በማሸነፉና ከአንድ በላይ ኮንትራቶችን ለማሸነፍ ተጨማሪ የሚጠበቅበትን መስፈርት ማሟላት አልቻለም:: ስለሆነም ውሉ ለ2ኛው ከፍተኛ ውጤት ላገኘው ተጫራች እንዲሰጥ ሆኗል፣ |
| 5. | አርኮን ዲዛይን እና ግንባታ ኃ/የተ/የግ/ማ | በቴክኒክ ግምገማ ወቅት ብቁ አይደለም | የፋይናንሺያል ጨረታ ሰነድ አልተከፈተም | | |

ሁለተኛው የጨረታ ግዥ በተመሳሳይ በግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ **ሰኔ 03/2014 ዓ.ም** በቁጥር W/52/ICB/OC/GOE/2014 EFY እንደወጣ የጨረታ ሰነዱ የሚያመላክት ሲሆን 3 ተጫራቾች ሞልተው መልሰዋል፡፡ **ነሀሴ 24/2014 ዓ.ም** ጨረታው ተከፍቶ 1 ተጫራች ለፋይናንሻል አልፎ **"አለማየሁ ከተማ ጀነራል ኮንትራክተር"** አሸናፊ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በሚከተለው ሠንጠረዥ የሥራ ተቋራጮች ውጤት ቀርቧል፡፡

**የአጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሌራ ሠንጠረዥ ሁለተኛ ጊዜ የተቋራጭ ጨረታ 3፡-**

| ተ.ቁ | የሥራ ተቋራጭ ስም | ቴክኒካል/% | ፋይናሽያል ብር |
|---|---|---|---|
| 1. | አለማየሁ ከተማ አጠቃላይ ስራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግ/ማ | የብቃት መስፈርቱን ያሟላል | 5,106,525,491.61 |
| 2. | ሳትኮን ኮንትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ | በቴክኒክ ግምገማ ወቅት ብቁ አይደለም | የፋይናንሺያል ጨረታ ሰነድ አልተከፈተም |
| 3. | ዬንኮምድ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ | በቴክኒክ ግምገማ ወቅት ብቁ አይደለም | የፋይናንሺያል ጨረታ ሰነድ አልተከፈተም |

ለሁለተኛ ጊዜ ለአማካሪ ነሐሴ 16/2012 ዓ.ም በጨረታ ቁጥር S/28/NCB/RP/GOE/ 2013 EFY በወጣው 6 ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሰነድ ሲገዙ 5 ተወዳዳሪዎች ሞልተው አስገብተዋል 5ቱም ለፋይናንሻል ያለፉ ሲሆን "አይዲኮን ኢንፍራስትራክቸር ዴቨሎፕመንት ኮንሰልታንትስ ኃ/የተ/የግ/ማ" ሰኔ 8/2013 ዓ.ም ዝቅተኛ ዋጋ በብር 21,552,782.50 (ሃያ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ሰማንያ ሁለት ከ50/100) በማቅረቡ አሸንፏል፡፡ የአማካሪዎች ውጤት በሚከተለው ሰንጠረዥ 4 ቀርቧል፡፡

**የአጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሌራ የሁለተኛ የአማካሪ ግዥ ጨረታ ሠንጠረዥ 4፡-**

| ተ.ቁ | የአማካሪ መሐንዲሶች ስም | ቴክኒካል/% | ፋይናሽያል ብር | ጠቅላላ ነጥብ ከ100 | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ኮር ኮንሰልታንት ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማ | 73.28 | 35,072,700.00 | 83.19 | |
| 2. | ኤልዳ ምህንድስና አማካሪዎች ከደምራ አማካሪ መሐንዲሶች ኃ.የተ.የግ.ማ | 68.86 | 22,092,230.25 | 84.60 | |
| 3. | ፎርትረስ ኢንጂነሪንግ ኮንሰልታንትና አሶሴት ኃ/የተ/የግ/ማ | 69.06 | 17,379,646.53 | 89.06 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| **4.** | **አይዲኮን ኢንፍራስትራክቸር ዴቨሎፕመንት ኮንሰልታንትስ ኃ/የተ/የግ/ማ** | **73.28** | **21,778,930.00** | **89.24** | በኮንትራት ድርድር ወቅት፣ የጨረታ ሰንዱ በሚጠይቀው መስፈርት መሰረት፣ በጨረታ ሂደት ወቅት የተገመገመውንና በመ/ቤቱ ተቀባይነት ያገኘውን ተጠሪ መሐንዲስ ውል ከመፈረሙ በፊት በድርጅቱ ጥያቄና ግለሰቡ በፕሮጀክቱ ላይ መስራት ባለመቻሉ በምትኩ ለተጠሪ መሐንዲስነት የቀረበው ግለሰብ ቀድሞ ከቀረበው አነስተኛ ነጥብ በማምጣቱ ምክንያት ከዋጋው ብር **226,147.50** ተቀናሽ ተደርጓል፡፡ የውል ስምምነቱ በብር **21,552,782.50** ተፈርሟል፡፡ |
| 5. | ኤስጂ ኮንሰልታንት ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማ | 74.46 | 25,372,162.50 | 88.16 | |

### 2. የወራቤ-ቦጀበር የመንገድ ፕሮጀክት፡-

***ይህ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሆኖ በስልጤ ዞን ከወራቤ ከተማ የሚነሳ እና ዝግባው፣ ኩተሬ፣ አብጀት፣ ተከሶ፣ ከከቶ አዲስ ገበያ እና ተረጋ ከተማዎችን የሚያገናኝና 3 ወረዳዎችን የሚያቋርጥ ሲሆን 38.5 ኪ.ሜ ይሸፍናል፡፡ መንገዱ ቡታጅራ ወራቤ ሆሳዕና መንገድና ቡታጅራ ቦጀበር እንድብር ሆሳዕና የሚያገናኝ መንገድ ነው፡፡***

***የመጀመሪያው*** በጨረታ ቁጥር W/33/NCB/OC/GOE/2007EFY **ግንቦት 07/2007 ዓ.ም** በኢትዮጵያ ሔራልድ ጋዜጣ እና በዌብ ሳይት በግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶ 35 ተወዳዳሪዎች ገዝተው **ህዳር 09 ቀን 2008 ዓ.ም** ሲከፈት 16 ተወዳዳሪዎች ሞልተው መመለሳቸውን፣ 11 ቴክኒካል፣ 9 ፋይናሻል ከተወዳደሩት ውስጥ 5 በቴክኒካልና ፋይናሻል ማለፋቸውን፣ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው **"የማነ ግርማይ ጀነራል ኮንትራክተር"** ማለፉን፣ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ከአፍሪካ ኢንሹራንስ ብር **45,344,565.00** (አርባ አምስት ሚሊዮን ሦስት መቶ አርባ አራት ሺህ አምስት መቶ ስልሳ አምስት) ማቅረቡን እና የአማካሪው ድርጅት **"ሲቪል ሥራዎች አማካሪ መሐንዲሶች ኃ.የተ.የግ.ማ"** በጨረታ ቁጥር S/20/NCB/RP/GE/ 2008 EFY ማሸነፉን የሰነድ ማስረጃዎች ያሳያሉ፡፡

**ወራቤ-ቦጀበር የመጀመሪያ የጨረታ ሠንጠረዥ 1፡-**

| ተ.ቁ | የሥራ ተቋራጭ ስም | ቴክኒካል/% | ፋይናሽያል ብር |
|---|---|---|---|
| 1. | አዋሽ ወልዳይ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግ/ማ | የብቃት መስፈርቱን ያሟላል | 643,439,951.07 |
| 2. | የመከላከያ ኮንስትራክሽን ድርጅት ኃ/የተ/የግ/ማ | የብቃት መስፈርቱን ያሟላል | 725,711,875.28 |
| 3. | ድሪባ ደፈርሻ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግ/ማ | የብቃት መስፈርቱን ያሟላል | 618,497,600.00 |
| 4. | ፋል አጠቃላይ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግ/ማ | የብቃት መስፈርቱን ያሟላል | 848,664,838.20 |
| 5. | ራማ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ | የብቃት መስፈርቱን ያሟላል | 787,794,786.75 |
| 6. | ሼድ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግ/ማ | የብቃት መስፈርቱን ያሟላል | 514,333,741.02 |
| 7. | ሰንሻይን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ | የብቃት መስፈርቱን ያሟላል | 609,094,550.00 |
| **8.** | **የማነ ግርማይ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግ/ማ** | **የብቃት መስፈርቱን ያሟላል** | **458,445,650.00** |
| 9. | ዮቴክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ | የብቃት መስፈርቱን ያሟላል | 649,750,991.00 |
| 10. | ክሮስላንድ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ | በቴክኒክ ግምገማ ወቅት ብቁ አይደለም | የፋይናንሺያል ጨረታ ሰነድ አልተከፈተም |
| 11. | ዲኤምሲ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ | በቴክኒክ ግምገማ ወቅት ብቁ አይደለም | የፋይናንሺያል ጨረታ ሰነድ አልተከፈተም |
| 12. | እሸቱ ለማ መንገድ ግንባታ ኃ/የተ/የግ/ማ | በቴክኒክ ግምገማ ወቅት ብቁ አይደለም | የፋይናንሺያል ጨረታ ሰነድ አልተከፈተም |
| 13. | ኢትዮ - ካናዳ ቢዝነስ ግሩፕ ኃ/የተ/የግ/ማ | በቴክኒክ ግምገማ ወቅት ብቁ አይደለም | የፋይናንሺያል ጨረታ ሰነድ አልተከፈተም |
| 14. | ሄኖክ እና ቤተሰብ አጠቃላይ ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማ | በቴክኒክ ግምገማ ወቅት ብቁ አይደለም | የፋይናንሺያል ጨረታ ሰነድ አልተከፈተም |
| 15. | ማርካን ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ | በቴክኒክ ግምገማ ወቅት ብቁ አይደለም | የፋይናንሺያል ጨረታ ሰነድ አልተከፈተም |
| 16. | ፓወርኮን ኃ/የተ/የግ/ማ | በቴክኒክ ግምገማ ወቅት ብቁ አይደለም | የፋይናንሺያል ጨረታ ሰነድ አልተከፈተም |

**የአማካሪዎች የጨረታ ውድድር ውጤት፤**

**ወራቤ-ቦጀበር የመጀመሪያ የአማካሪ የጨረታ ሠንጠረዥ 2፡-**

| ተ.ቁ | የአማካሪ መሐንዲሶች ስም | ቴክኒካል/ % | የተገመገመ የፋይናንስ ፕሮፖዛል ጊዜያዊ ድምር ተጠባባቂ በጀት (PS) ሳይጨምር | ተጠባባቂ በጀት (PS) | ጠቅላላ ነጥብ ከ 100 | ማብራሪያ (አጠቃላይ ዋጋ) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ብርሃን ኮንስትራክሽን ዲዛይን | 67.7 | 19,219,228.00 | 1,500,000 | 79.0 | |
| **2.** | **ሲቪል ስራዎች አማካሪ መሐንዲሶች ኃ.የተ.የግ.ማ** | 69.9 | 18,465,211.85 | 1,500,000 | 81.7 | የውል ስምምነቱ ተጠባባቂ በጀትን (PS) ጨምሮ ተፈርሟል። በዚህም መሰረት አጠቃላይ የኮንትራት መጠኑ በብር 19,965,211.85 ይሆናል፡፡ |
| 3. | ሲም አማካሪዎች ኃ.የተ.የግ.ማ | 59.0 | 10,896,839.00 | 1,500,000 | 79.0 | |
| 4. | ትራንስናሽናል መሐንዲሶች ኃ.የተ.የግ.ማ | 67.8 | 21,335,550.00 | 1,500,000 | 78.0 | |
| 5. | የርየር ኢንጂነሪንግ ኃ.የተ.የግ.ማ ከኋይትናይት ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት አማካሪዎች ከ CIBAR (ንዑስ አማካሪ) ጋር | 67.0 | 20,306,300.00 | 1,500,000 | 77.7 | |

**ሁለተኛው** የፕሮጀክቱ ጨረታ ቁጥር W/21/NCB/OC/GOE/2011EFY **ታህሳስ 12/20011 ዓ.ም** በኢትዮጵያ ሔራልድ ጋዜጣ እና በዌብ ሳይት በቀረበ ማስታወቂያ 6 ተወዳዳሪዎች የገዙ ሲሆን **ጥር 1/2011 ዓ.ም** 5 ተወዳዳሪዎች ሞልተው ሲመልሱ ለፋይናሻል 2 ድርጅቶች ማለፋቸውን፣ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው **"ማርካን ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ"** አሸናፊ መሆናቸውንና የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና አባይ ኢንሹራንስ ብር **79,500.000** (ሰባ ዘጠኝ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ) ማቅረባቸውን የሰነድ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ የሥራ ተቋራጮች የጨረታ ውጤት በሚከተለው ሠንጠረዥ ተመላክቷል፡፡

**ወራቤ-ቦጆበር የሁለተኛ የተቋራጮች ጨረታ ሠንጠረዥ 3፡-**

| ተ.ቁ | የሥራ ተቋራጭ ስም | ቴክኒካል/% | ፋይናሽያል ብር |
|---|---|---|---|
| 1. | ራማ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ | የብቃት መስፈርቱን ያሟላል | 857,747,734.17 |
| **2.** | **ማርካን ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ** | **የብቃት መስፈርቱን ያሟላል** | **795,000,000.00** |
| 3. | አለማየሁ ከተማ ኃ/የተ/የግ/ማ | በቴክኒክ ግምገማ ወቅት ብቁ አይደለም | የፋይናንሺያል ጨረታ ሰነድ አልተከፈተም |
| 4. | ቤኤካ አጠቃላይ ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማ | በቴክኒክ ግምገማ ወቅት ብቁ አይደለም | የፋይናንሺያል ጨረታ ሰነድ አልተከፈተም |
| 5. | ኪቢሽ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ | በቴክኒክ ግምገማ ወቅት ብቁ | የፋይናንሺያል ጨረታ ሰነድ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | አይደለም | አልተከፈተም |

**ለሁለተኛው** ጊዜ በጨረታ ቁጥር S/15/NCB/RFP/GOE/2011 EFY ለአማካሪ ውድድር ቴክኒክንና ፋይናሽያል 4 ተወዳዳሪዎች ያለፉ ሲሆን ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው **"ስታዲያ የምህንድስና ስራዎች አማካሪዎች ኃ/የተ/የግ/ማ"** መሆኑን ሰነዱ ይገልፃል፡፡

**ወራቤ-ቦጆበር ሠንጠረዥ 4፡-**

| ተ.ቁ | የአማካሪ መሐንዲሶች ስም | ቴክኒካል በ% | ፋይናሽያል በብር | ጠቅላላ ነጥብ ከ100 |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ኮር አማካሪ መሐንዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማ | 73.02 | 24,614,634.50 | 88.01 |
| 2. | ኔት መሐንዲሶች እና አርክቴክቶች ኃ/የተ/የግ/ማ | 73.51 | 23,558,089.25 | 89.17 |
| **3.** | **ስታዲያ የምህንድስና ስራዎች አማካሪዎች ኃ/የተ/የግ/ማ** | **73.12** | **18,451,520.00** | **93.12** |
| 4. | ዩናይትድ አማካሪ መሐንዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማ | 71.25 | 19, 668, 371.43 | 90.01 |

**ለሦስተኛው** ርዝመት **41.35 ኪ.ሜ** በሚል የጨረታ ቁጥር **W/45/NCB/DA/ GOE/2015 EFY** ያለ ቢሆንም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 51(1(ረ) በጣም አስቸኳይ ከመሆኑ የተነሳ ከባድ ችግር የሚፈጥርና በመ/ቤቱ ሥራ አፈፃፀም ላይ ጉዳትን የሚያስከትል በመሆኑ ምክንያት በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የተፈቀደ ግዥ፤ በሚለው አንቀጽ በቀጥታ ግዥ **ከአማራ መንገድ ሥራዎች ኢንተርፕራይዝ** ጋር የተካሄደ ሲሆን ውጤቱም በሚከተለው ሠንጠረዥ ተመላክቷል፡፡

**ወራቤ-ቦጆበር ሠንጠረዥ 5፡-**

| ተ.ቁ | የሥራ ተቋራጭ ስም | ቴክኒካል/% | ፋይናሽያል ብር |
|---|---|---|---|
| 1. | የአማራ መንገድ ስራዎች ድርጅት | በቀጥታ የግዥ ሂደት ዘዴ የተገዛ | **2,777,252,940.36** |

**ለሦስተኛው** ጊዜ አማካሪዎች በጨረታ ቁጥር ERA-NCB-C-0035-2015 BID በኤሌክትሮኒክስ (e-GP) 6 ተወዳዳሪዎች የቀረቡ ሲሆን ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው **"ኤስ.ጂ. ኮንስልታንት ኢንጂነሪንግ ኃ.የተ.የግ.ማ"** ጋር **መስከረም 27 ቀን 2017 ዓ.ም** ግዥ ተፈጽሟል፡፡

**ወራቤ-ቦጆበር ሠንጠረዥ 6፡-**

| ተ.ቁ | የአማካሪ መሐንዲሶች ስም | ቴክኒካል/% | ፋይናሽያል ብር | ጠቅላላ ነጥብ ከ100 |
|---|---|---|---|---|

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ኢትዮ ኢንፍራ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማ | 74.70 | 22,905,700.00 | 85.53 |
| 2. | ጎጎት አማካሪ መሐንዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማ | 73.32 | 16,507,549.15 | 88.35 |
| 3. | ኋይትናይት ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት አማካሪዎች ኃ/የተ/የግ/ማ | 72.79 | 13,993,637.00 | 90.52 |
| **4.** | **ኤስ.ጂ. ኮንሰልታንት ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማ** | **74.76** | **12,401,743.75** | **94.76** |
| 5. | ፕሮሚነንት የምህንድስና ሶሉሽን ኃ/የተ/የግ/ማ | 76.16 | 17,625,585.00 | 90.23 |
| 6. | የተባበሩት አማካሪ መሐንዲሶች ከስማርት አማካሪ መሐንዲሶች ጋር በንዑስ አማካሪ | የቴክኒክ መስፈርቶችን አያሟላም | የፋይናንሺያል ጨረታ ሰነድ አልተከፈተም | |

### 4.3 የውል አስተዳደር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 ዓ.ም መሠረት የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 247/2003 አንቀጽ 7(7) መሠረት አስተዳደሩ የሥራና የአማካሪነት አገልግሎት ውሎችን ያዘጋጃል፣ እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ይዋዋላል፣ ሥራዎች በውላቸው መሠረት የሚከናወኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በበላይነት ይቆጣጠራል ወይም በሌላ አካል ቁጥጥር እንዲካሄድ ያደርጋል፤ በሚለው ድንጋጌ መሠረት የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የመንገድ ፕሮጀክቶችን በሚመለከት የመንግስት የውል ህግ እና የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር መሠረት በማድረግ ዝቅተኛ ዋጋ ካቀረቡት ሥራ ተቋራጮች እና ከአማካሪዎች ጋር ውል መዋዋሉን በሰነድ መረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል፤ ነገር ግን በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት የሚመረጡበትን ዘዴ በአግባቡ ባለመወሰኑና ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል ባለማድረጉ በሥራ ተቋራጮች ደካማ አፈፃፀም ምክንያት የመጀመሪያውና የሁለተኛው ውሎች እንዲቋረጡ ስለመደረጉ ከዚህ በታች ተመላክቷል፡፡

#### 1. የአጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሴራ የመንገድ ፕሮጀክት፡-

**በመጀመሪያው** ውል የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር **97 ኪ.ሜ** ለመሥራት ግንቦት 15/2009 **ዓ.ም ከሻንዶግ ሃይዌይ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን** ፕሮጀክቱን **በ42 ወራት** ውስጥ ሰርቶ በማጠናቀቅ ለማስረከብ ውል እንደገባ በግልጽ ተመልክቷል፡፡

**የመጀመሪያው** **ከኋይትናይት ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኮንሰልታንት** ኃ/የተ/የግ/ማ ጋር **መስከረም 30/2010 ዓ.ም** ጋር የአማካሪነት ውል ተፈጽሟል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ውሎች መሰረት የሥራ ተቋራጩ ሥራውን አጠናቆ አላስረከበም፤ አፈፃፀሙም **25.96 ፊዚካል እና 31.90% ፋይናንሽያል** መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር በፕሮጀክት አስተዳደር እና በሳይት ሀብት ቅንጅት ደካማ አፈጻጸም፣ አግባብ ያልሆነ የገንዘብ ፍሰት፣ የማቴሪያል ግምገማ በወቅቱ አለማድረግ እና በአጠቃላይ የኮንትራክተሩ ደካማ አፈፃፀም እንዳለ በመግለጽ ለስራ ተቋራጩ በቀን **ህዳር11/2013 ዓ.ም** በደብዳቤ ቁጥር 451/39/3-121 የውል ማቋረጥ ደብዳቤ የተፃፈ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

**ለሁለተኛ ጊዜ** በወጣው ጨረታ **ህዳር 7/2015 ዓ.ም** **አለማየሁ ከተማ አጠቃላይ ኮንትራክተር በ38 ወራት** ሰርቶ ለማጠናቀቅ ብር **510,652,594.16** (አምስት መቶ አስር ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ዘጠና አራት ከ16/100) ለስራ ዋስትና ገንዘብ በማስያዝ እንደገባ በውሉ ላይ ተመላክቷል፡፡

**የሁለተኛው አማካሪ** **አይዲኮን ኢንፍራስትራክቸር ዴቨሎፐመንት ኮንሰልታንት** ኃ/የተ/የግ/ማ **ሰኔ 8/2013 ዓ.ም** የአማካሪነት ውል ተዋውሏል፡፡

በአጠቃላይ የመንገድ ፕሮጀክቱ **ሰኔ ወር 2017 ዓ.ም** መጨረሻ **32.37 ፊዚካል እና 49% ፋይናንሻል አፈፃፀም** ላይ እንደሚገኝ ከመረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

## 2. የወራቤ-ቦጀበር፡-

**የመጀመሪያው** አሸናፊ **"የማነ ግርማይ ጀነራል ኮንትራክተር"** ሥራ ተቋራጭ **ግንቦት 12/2008 ዓ.ም በ3 ዓመት እና ተጨማሪ 3 ወራት** ውል መዋዋሉን የሰነድ ማስረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

ይሁን እንጂ ሥራ ተቋራጩ **እስከ ሐምሌ 20/2009 ዓ.ም** ለሠራተኞች ደመወዝ መክፈል ባለመቻሉ **እስከ መስከረም 8/2010 ዓ.ም** ሠራተኞች ወደ ሥራ ባለመመለሳቸው **መጋቢት 21 ቀን 2009 ዓ.ም** ጀምሮ ሥራውን በማቆማቸው በቁጥር AS1/15/1-64 **ታህሳስ 9 ቀን 2010 ዓ.ም** በአንድ ሳምንት ውስጥ ሥራውን እንዲቀጥሉ ትዕዛዝ መተላለፉን፤ **መስከረም ወር 2011 ዓ.ም** በአፈፃፀም ላይ ምንም ማሻሻያ ሳያደርግ በደብዳቤ ቁጥር MM3/294/20-3334 እስከ **ጥር 8 ቀን 2010 ዓ.ም** ለመስራት ምንም ዓይነት ፕሮፖዛል ባያቀርቡም፣ ለሥራው ፍላጎት ባያሳዩም ለሥራ ተቋራጩ የ14 ቀን ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ በውል አንቀጽ 15.2 መሠረት **የካቲት 22**

**ቀን 2010 ዓ.ም የሥራ ውሉ መቋረጡን፤** ውሉ ሲቋረጥ **ፊዚካል 2.88 ኪ.ሜ እና ፋይናንሽያል 7.1% አፈፃፀም** ሆኖ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የሰነድ መረጃ የሚያሳይ ሲሆን በሌላ በኩል ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን የተገኘ መረጃ ደግሞ ውሉ ሲቋረጥ **ፊዚካል 5.71 ኪ.ሜ እና ፋይናንሻል 7.11%** አፈጻጸም እንደሆነ ያሳያል፡፡

**የመጀመሪያው** **ሲቪል ስራዎች አማካሪ መሐንዲሶች ኃ.የተ.የግ.ማ ታህሳስ 28/2009 ዓ.ም** የሥራ ውል ከአሰሪው መ/ቤት ጋር ተፈራርሟል፡፡

**ሁለተኛው** ውል **ከማርካን ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ** ሥራ ተቋራጩ ጋር **ሐምሌ 11/2011 ዓ.ም** ፕሮጀክቱን 3 ዓመት **ከ 3 ወር ቀናት** ለማጠናቀቅ መዋዋላቸውንና ፕሮጀክቱም ጥር 17 ቀን 2012 ዓ.ም መጀመሩን የሰነድ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

**ሁለተኛው** ስታዲያ የምህንድስና ስራዎች አማካሪዎች ኃ/የተ/የግ/ማ አሽናፊ አማካሪ ደግሞ **ጳጉሜ 5/2011 ዓ.ም** የሥራ ውል ተፈራርሟል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ውሎች ቢፈፀሙም ሁለተኛው ሥራ ተቋራጭ ቀሪ ሥራዎችን በአግባቡ ሊሰራ ባለመቻሉ አሰሪው መ/ቤት በቁጥር S.A.D/W.B/058/22 ለማስተካከል የ1 ወር ጊዜ ቢሰጠውም ለመስራት ፍላጎት ባለማሳየቱ ውሉ ተቋርጧል፡፡ ውሉ ሲቋረጥ **ፊዚካል 16.84 ኪ.ሜ ፋይናንሽያል 40.77 %** አፈፃፀም መሆኑን የመ/ቤቱ መረጃዎች ያሳያሉ፤ **ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን** የተገኘ መረጃ ደግሞ የሥራ ውሉ ሲቋረጥ **ፊዚካል 40.78 ኪ.ሜ ፋይናንሻል 40.77 %** አፈፃፀም ያሳያል፡፡

**የሦስተኛው ውል የአማራ መንገድ ሥራዎች ድርጅት** (የአሁኑ **ህብር ኮንስትራክሽን ኮርፕሬሽን**) ጳጉሜ 2 ቀን 2015 ዓ.ም ፕሮጀክቱን **በ2 ዓመት እና በተጨማሪ 3 ወር** ለመጨረስ ተዋውለው የዋስትና ማስከበሪያ ከአባይ ኢንሹራንሽ ብር 277,725,294.00 (ሁለት መቶ ሰባ ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃያ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና አራት) በማስያዝ ከመስከረም 23 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ የተጀመረ ሲሆን ሰኔ ወር 2017 ዓ.ም የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር **ፊዚካል 34.86% ሲሆን ፋይናንሽያል 49%** መሆኑን መረጃው ያሳያል፣ በአማራ መንገድ ሥራዎች ሥራ ተቋራጭ መሐንዲስ መግለጫ እስከ ጥር 30 ቀን 2017 ዓ.ም መጨረሻ **54.4%** መድረሱን ቢጠቁሙም ከሪፖርቱ ጋር አይጣጣምም፡፡

**ሶስተኛው ኤስ.ጂ. ኮንሰልታንት ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማ አማካሪ መስከረም 27 ቀን 2017 ዓ.ም**

የሥራ ውል የተዋዋለ ሲሆን የዋስትና ማስከበሪያ ከአባይ ኢንሹራንስ ብር 83,096.68 (ሰማንያ ሦስት ሺህ ዘጠና ስድስት 68/100) ከአሰሪ መ/ቤቱ ጋር ተፈራርመዋል፡፡

| በጥናቱ በናሙና የታዩ 2 ፕሮጀክቶች የውል ሁኔታ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | ፕሮጀክቱ ስም | የፕሮጀክት ስራ ተቋራጭ | የመጀመሪያ የውል ጊዜ | ውል የሚጠናቀቅበት ጊዜ | ውሉ የተቋረጠበት ጊዜ |
| 1 | አጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሴራ | 1.1 ሻንዶግ ሃይ ዌይ ኢንጂነሪንግ | ግንቦት 15/2009 ዓ.ም | ጥቅምት 15/2013 | ህዳር 11/2013 ዓ.ም |
| | | 1.2 አለማየሁ ከተማ ጀነራል ኮንትራክተር | ህዳር 7/2015 ዓ.ም | ጥር 7/2018 ዓ.ም | በመሥራት ላይ |
| 2 | ወራቤ-ቦጀበር | 2.1 የማነ ግርማ ጀነራል ኮንትራክተር | ግንቦት 12/2008 | ነሐሴ 12/2011 | የካቲት 22/2010 ዓ.ም |
| | | 2.2 ማርካን ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ | ሐምሌ 11/2011 | ጥቅምት 2015 ዓ.ም | ታህሳስ 7/2015 ዓ.ም |
| | | 2.3 የአማራ መንገድ ሥራዎች | ከመስከረም 23 ቀን 2016 ዓ.ም | ታህሳስ 2017 | በመሥራት ላይ |

| በጥናቱ በናሙና የታዩ 2 ፕሮጀክቶች የውል በጀትና ተጨማሪ የተጠየቀ በጀት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | ፕሮጀክቱ ስም | የፕሮጀክት ስራ ተቋራጭ | የውል በጀት | በልዩነት ተጨማሪ በጀት |
| 1 | አጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሴራ | 1.1 ሻንዶግ ሃይ ዌይ ኢንጂነሪንግ | 1,165,299,596.00 | 3,941,226,345.61 |
| | | 1.2 አለማየሁ ከተማ ጀነራል ኮንትራክተር | 5,106,525,941.61 | |
| 2 | ወራቤ-ቦጀበር | 2.1 የማነ ግርማ ጀነራል ኮንትራክተር | 458,445,650.00 | 2,318,807,290.36 |
| | | 2.2 ማርካን ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ | 795,000,000.00 | |
| | | 2.3 የአማራ መንገድ ሥራዎች | 2,777,252,940.36 | |

| በጥናቱ በናሙና የታዩ 2 ፕሮጀክቶች የአማካሪ ድርጅቶች ውል | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የፕሮጀክት ስም | የአማካሪ ድርጅቶች ስም | የውል ጊዜ | የውል በጀት | አጠቃላይ በጀት (ተጨማሪ ወጪ) |
| 1 | አጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ- | 1.1 ኋይትናይት ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት አማካሪዎች ኃ/የተ/የግ/ማ | ጥር 25/2009 ዓ.ም | 20,670,100.00 | 1,108,830 (አጠቃላይ በጀት |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ኮሴ-ጌጃ-ሴራ | 1.3 አይዲኮን ኢንፍራስትራክቸር ዴቨሎፐመንት ኮንሰልታንትስ ኃ/የተ/የግ/ማ | ሰኔ 8/2013 ዓ.ም | 21,778,930.00 | 42,449,030.00 ) |
| 2 | ወራቤ-ቦጆበር | 2.1 ሲቪል ስራዎች አማካሪ መሐንዲሶች ኃ.የተ.የግ.ማ | ግንቦት 12/2008 | 19,965,211.85 | አጠቃላይ በጀት 50,818,475.60 |
| | | 2.2 ስታዲያ የምህንድስና ስራዎች አማካሪዎች ኃ/የተ/የግ/ማ | ሐምሌ 11/2011 | 18,451,520.00 | |
| | | 2.3 ኤስ.ጂ. ኮንሰልታንት ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማ | መስከረም 27/2017 ዓ.ም | 12,401,743.75 | |

በናሙናነት በተመረጡት የአጣጥ ዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሌራ የመንገድ ፕሮጀክት የአዋጭነት ጥናት የተካሄደ ሲሆን የወራቤ-ቦጆበር የመንገድ ፕሮጀክት የአዋጭነት ጥናት ስለመካሄዱ መረጃ አልተገኘም፡፡ ይህም የመንገድ ስራ ፕሮጀክቶቹ በወጪ፣ በገንዘብ፣ በጥራት እና የሕብረተሰቡን ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አኳያ በፕሮጀክቶቹ ዙሪያ የተስተዋሉ የአሠራር ክፍተቶች እንዲፈጠሩ ያደረገ ስለመሆኑ ከመረጃዎቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡

የወሰን ማስከበር የካሳ ክፍያን በተመለከተ የአጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሌራ የመንገድ ፕሮጀክት ብር 229,100,000 (ሁለት መቶ ሃያ ዘጠኝ ሚሊዮን **አንድ መቶ ሺህ**) ክፍያ ተፈጽሟል፡፡ ቀሪ ያልተከፈለ ብር **41,706,585.31** (አርባ አንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሰማንያ አምስት 31/100)፣ **የወራቤ-ቦጆበር** ብር 123,848,000.00 (አንድ መቶ ሃያ ሦስት ሚሊዮን ስምንት መቶ አርባ ስምንት ሺህ) ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን ቀሪ ብር **188,094,000.04** (አንድ መቶ ሰማንያ ስምንት ሚሊዮን ዘጠና አራት ሺህ ከ04/100) ያልተከፈለ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

### 4.3.1 ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ

የቃለ መጠይቅ አንዱ የጥናት መረጃ መሰብሰቢያ ስልት ሲሆን፣ ይህ ጥናት በመንገድ ፕሮጀክቶች ከሚመደብለት ከፍተኛ በጀት አንፃር ለጥናቱ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የሚታመንባቸው ባለሙያዎችና የስራ ኃላፊዎች፣ የመንገድ ፕሮጀክት ሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች፣ በፕሮጀክቱ ስፍራ ከሚገኙ የአስተዳደር አካላት እና የአካባቢ ነዋሪዎች ጋር በግልና በቡድን ውይይት ተከናውኗል፡፡

በዚህ መሰረት የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 247/2003 ዓ.ም ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መካከል አንቀጽ 7(7) መሠረት የሥራ ተቋራጭና የአማካሪነት ውሎችን ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ይዋዋላል፣ ሥራዎችን በየውላቸው መሠረት የሚከናወኑ መሆናቸውን በበላይነት ይቆጣጠራል ወይም በሌላ አካል ቁጥጥር እንዲካሄድ ያደርጋል፣ ስለሚል ከዚህ አንፃር ለተዘጋጁ ቃለመጠይቆች የሚከተሉት ምላሾች ተሰጥተዋል፡-

- የመንገድ ፕሮጀክቶችን ለመስራት የታቀደ እቅድ በፕላን ሚንስቴር ከፀደቀ በኋላ የዲዛይን ሥራ እንደሚከናወን፣ በአማካሪ መሐንዲስ አማካኝነት በግዥ መመሪያው መሰረት የጨረታ ግዥ እንደሚዘጋጅ፣ አስቀድመው ለሁለት ቀን የግዥ ጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት ለሥራ ተቋራጮች እንደሚያስተዋውቁ፣ የጨረታ ውጤቱ ለሁሉም እኩል በደብዳቤ እንደሚሰጣቸው፣ አማካሪዎች የካምፓኒያቸው መረጃ (Profile) ታይቶ የተሻለ አቅምና ብቃት ያላቸውን በማወዳደር እንደሚመርጡ፣ ቅሬታ እስከ 5 ቀናት ማቅረብ እንደሚቻሉ፣ ቀጥሎም በተቋቋመው ቦርድ አማካኝነት የሚፀድቅ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

- የአማካሪ ውሎችን በሌላ አካላት እንዲዘጋጅ የሚደረግ ከሆነ በራሳቸው ነፃና ገለልተኛ (Independent) በሆኑ ድርጅቶች ይዘጋጅ እንደነበር ተጠቁመው አሁን ግን በመ/ቤታቸው ብቻ እንደሚዘጋጅ ጠቅሰዋል፤ በሌላ አካል ቁጥጥር የሚደረግ ከሆነ ነፃና ገለልተኛ (Independent) በሆነ ድርጅት ቁጥጥር የሚካሄድ መሆኑን አስረድተዋል፡፡
- በየሳምንቱ በሚደረገው ውይይት፣ በወርሃዊ ሪፖርትና በመሬት ላይ ባለው ምልከታ በሥራ ተቋራጭ ላይ የአፈፃፀም ክፍተት ካለ እንዲያስተካክል ምክር ከተሰጠው በኋላ የማያሻሽል ከሆነ ውል እስከ ማቋረጥ የሚደርስ እርምጃ እንደሚወሰድ አብራርተዋል፡፡
- ዝቅተኛ አፈፃፀም እንዲኖራቸውና ለረጅም ጊዜ እንዲዘገዩ ከሚያደርጋቸው ምክንያቶች መካከል የተቋራጭ የአቅም ውስንነት፣ የግብዓት አቅርቦት እጥረት፣ የክፍያ መዘግየት፣ የዋጋ ግሽበት፣ ወዘተ. መሆናቸውን ጠቅሰው በየወሩ እየተገመገመ ያላቸውን አፈፃፀም እየታየ እንዲቀጥሉና እንዳይቀጥሉ የሚወሰን መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡
- የመንግስትን ተጨማሪ ወጪ ለማስቀረት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመው ወቅታዊ እርምጃ ያልተወሰደው በጦርነት ምክንያት የሥራ ተቋራጮች ሂሳባቸውን ማንቀሳቀስ ባለመቻላቸው መሆኑን ጠቁመው፣ አማራጩ ሌላ ጨረታ በማውጣትና ውል በማዘጋጀት ሥራውን ማስቀጠል መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው **አዋጅ ቁጥር 1263/2014 ዓ.ም በከተማና መሠረተ ልማት ሚንስቴር ሥልጣንና ተግባር** አንፃር አንቀጽ 31(1)(ሐ) ሀገራዊ የመንገድ መሠረተ ልማት ሥራዎች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታነትንና ፍትሐዊ ተደራሽነትን መሠረት ባደረገ መልኩ መከናወናቸውን ይከታተላል፤ 31(1)(ከ) በዲዛይን፣ በጨረታና፣ በኮንትራት ይዘት ላይ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ የሚሉ ንዑስ አንቀፆች ያሉ ሲሆን ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ተጠሪነቱ ለሚንስቴር መ/ቤቱ ከመሆኑ አኳያ የመንገድ ፕሮጀክቶችን በሚመለከት በእቅዱ መሠረት በትክክል ስለመከናወናቸው በምን መንገድ ትከታተላችሁ? የመንገድ ፕሮጀክቶችን በሚመለከት የተዘረጋው የተጠያቂነት ሥርዓት ምን ይመስላል? የመንገድ ፕሮጀክቶች የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ለመፍታት የተደረገ ድጋፍ ካለ? በተለይም በተደጋጋሚ እየተቋረጡ ለሚቀጥሉና መንግስትን ለከፍተኛ ወጪ የዳረጉ መንገዶች ላይ የተወሰደ እርምጃ ካለ ቢገለጽ በሚል ዘርፉን ለሚመሩት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሚከተሉት ምላሾች ሰጠዋል፡፡

በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የታቀደውን እቅድ ገምግመው የጋራ እቅድ አድርገው እንደሚሰሩ፣ በቋሚነት ክትትልና ድጋፍ እንደሚያደርጉ፣ ሊያልቁ የተቃረቡት መንገዶች ላይ በልዩ ትኩረት እንደሚሰሩ፣ ለመንገድ

ፕሮጀክቶች የተዘጋጀው መስፈርት ጠንካራ ስለሆነ የሀገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች ከፍተኛ የአቅም ውስንነት ያለባቸው በመሆኑና ብዙዎች የማያሟሉ በመሆናቸው በጨረታው ሳይመረጡ እንደሚቀሩ፣ በተደጋጋሚ የተቋረጡ መንገዶችን ለማስቀጠልና በአካባቢው ለሚገለገለው ህብረተሰብ መፍትሄ ለመስጠት የተሻለ አቅም ያላቸው የልማት ድርጅቶች እንዲሰሩ የውሳኔ ሀሳብ በማቅረብ መፍትሔ እንዲሰጣቸው መደረጉን፣ የካሳ ክፍያ እንዲስተካከል የህግ ማሻሻያ የተደረገ መሆኑን አብራርተዋል፡፡ በአቋራጭ ለመበልፀግ የሚሞክሩ የሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና መሐንዲሶች ለመከላከል አሠራራቸውን እያስተካከሉና እያዘመኑ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ለጥናቱ ሚና ካላቸው ተቋማት ውስጥ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን አንዱ ሲሆን ዘርፉን ከሚመሩት ም/ዋና ዳይሬክተር እና መሪ ሥራ አስፈፃሚ እንዲሁም ከአንድ ባለሙያ ጋር በቡድንና በተናጠል ውይይት ተደርጓል፡፡ በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 524/2015 ዓ.ም መሠረት ለባለሥልጣኑ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት መካከል በአንቀጽ 7(3) በዲዛይን፣ በጨረታ፣ በኮንትራት ይዘትና በውል አስተዳደር እንዲሁም በግንባታ ጥራት እና ቁጥጥር ግልፅና ተጠያቂነት ያለው የአሠራር ሥርዓት እንደሚዘረጋ፣ አፈፃፀሙን እንደሚከታተል፣ እንደሚያረጋግጥ፣ እንደሚቆጣጠር፤ በአንቀጽ 7(5) መሠረት ለመሰረተ ልማት ሥራዎች ግንባታ ሞዴል፣ ስፔስፊኬሽን፣ የልኬት ሥርዓትና ማንዋል እንደሚያዘጋጅ፤ እንደሚያረጋግጥ፤ እንደሚቆጣጠር፤ በአንቀጽ 7(6) በጨረታና ውል መሠረት በዲዛይን፣ በዋጋ፣ በጥራትና በጊዜ ተሰርተው ስለመጠናቀቃቸው እና ርክክብ ስለመደረጉ የመከታተል፣ የመቆጣጠር እና የእርምት እርምጃ እንደሚወስድ፤ በአንቀጽ 7(10) የግንባታ ሞዴል ዋጋዎች እና የግምት መስሪያ ቀመሮች እንደሚያዘጋጅ፤ የዋጋ ግምቶች በአግባቡ ስለመዘጋጀታቸው የመቆጣጠር፤ የማረጋገጥ፤ እንዲሁም በአንቀጽ 7(12) መሥራት ለሚችሉ ሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና በዘርፉ የሚሳተፉ ሌሎች ድርጅቶችን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት፤ የመቆጣጠር፣ የማገድ፣ የማሳገድ፣ የመሰረዝ፣ ወይም ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ የማድረግ፤ የሚሉ ንዑስ አንቀፆች አሉ፤ ከዚህ አንፃር ባለሥልጣኑ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የሚሰሩ የመንገድ ፕሮጀክቶችን በሚመለከት ምን ምን እንደሰሩ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የሚከተሉትን ምላሾች ሰጠዋል፡፡

ተቋሙ 2015 እንደ አዲስ የተቋቋመና የተደራጀ መሆኑን በመጠቀም በተሰጣቸው ሥልጣናን ተግባር መሠረት በሚፈለገው ደረጃ በትክክል አለመስራታቸውን ጠቅሰው፤ የፌደራል ዋና ኦዲተር በመንገድ ፕሮጀክቶች ላይ ያቀረበውን ችግር መነሻ በማድረግ የመስክ ምልከታ በማድረግ መፍትሔ ለመስጠት እንቅስቃሴ ላይ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

### 4.3.2 የኦዲት ቁጥጥር

ተቋሙ የውስጥ ኦዲት በየጊዜው ኦዲት እንደሚያደረግ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ "የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 5 ንዑስ ቁጥር 24 መሰረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ግዥ ሲፈጽሙ በውድድሩ ተሳታፊ የሚሆኑት አቅራቢዎች ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የሚመረጡ ሆኖ እስከተቻለ ድረስ ቁጥራቸው ከሶስት ማነስ እንደሌለበት ይደነግጋል፡፡

ይሁን እንጂ የመ/ቤቱ የ2016 ዓ.ም 4ኛ ሩብ ዓመት የውስጥ ኦዲት ሪፖርት በመንገድ ፕሮጀክት የግዥ አፈፃፀም የአሰራር ግድፈት የተለመደና በተደጋጋሚ የሚታይ የግዥ መመሪያ ጥሰት ከመሆኑም ባለፈ ለብልሹ አሰራር መንገድ የሚከፍት በመሆኑ አሰራሩ ሊታረም ይገባል፡፡" የሚል አስተያየት መቅረቡን የኦዲት ሪፖርት ሰነድ ያመላክታል፡፡

**የፌደራል ዋናው ኦዲተር የ2015 የኦዲት ሪፖርት** እንደሚያመላክተው በናሙና ከታዩ 10 የተቋረጡ የመንገድ ፕሮጀክቶች ውስጥ **የ9 ፕሮጀክቶች** ለመንግሥት ገቢ መደረግ የነበረበት **1,301,857,648.25** ለተቋራጮች የተከፈለ የቅድመ ክፍያ እና የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ ያልተደረገ ስለመሆኑ መረጃው ይገልፃል፡፡

በናሙና ከታዩ 10 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ ተመልሰው ወደ ግንባታ የገቡ 4 የመንገድ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ ባለመደረጉ በተደረገ ውለታ የመጀመሪያ የውል ዋጋ ብር **3,947,579,832.16** በድጋሚ ከሌላ ኮንትራክተር ጋር በተገባው የውል ዋጋ ብር **12,436,021,306.72** ሲሆን **ልዩነት ብር 8,488,441,474.56** ከፍተኛ የገንዘብ ልዩነት መኖሩ ያሳያል፡፡

በተጨማሪ **የ2016 የኦዲት ሪፖርት** በናሙና ካያቸው **296 የመንገድ ፕሮጀክቶች** ውስጥ 4 ዓመትና ከዚያ በላይ የዘገዩ እና ከዚህ ውስጥ **127** ፕሮጀክቶቹ ያሉበትን ደረጃ የሚያሳይ *መረጃ ያልተገኘላቸው* መሆኑ፤ **ከ267** ቢሊዮን ብር በላይ ተጨማሪ በጀት የጠየቁ መሆኑ፣ በእቅድ ከተያዘ በጀት **ብር 13.2** ቢሊዮን በላይ ተጨማሪ በጀት የወጣባቸው **ከ180 በላይ** የመንገድ ፕሮጀክቶች መኖራቸው፤ ከዚህ ውስጥ **ከ75 በመቶ በላይ ተጨማሪ ወጪ** የወጣላቸው የመንገድ ፕሮጀክቶች መኖራቸውን የፌደራል ዋናው ኦዲተር ሪፖርት ያሳያል፡፡

### 4.3.3 የመስክ ምልከታ

ለጥናቱ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎችን ለማሰባሰብ አንዱ ስልት ቃለ መጠይቅ ሲሆን ይህን መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የቡታጅራ አካባቢ ግንባታ ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ፣ የመንገድ ሥራ ተቋራጭ መሐንዲሶች፣ የመንገድ ሥራ አማካሪ መሐንዲሶች፣ የአካባቢው መስተዳደር አካላት ኃላፊዎች እና የአካባቢ ነዋሪዎች ላይ ትኩረት በማድረግ እና በአካል መንገዱን በመመልከት መረጃው ተሰብስቧል፡፡

1. የአጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሌራ የመንገድ ፕሮጀክት፡-




TOYOTA



### 1.1 በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ለቡታጅራ አካባቢ ግንባታ ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ እና ሳይት መሐንዲሶች የቀረበ ቃለመጠይቅ፡-

ለቀረበላቸው የተለያዩ ጥያቄዎች የሚከተሉትን ምላሾች ተሰጠዋል፤

የአጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሌራ መንገድ የተመረጠው የአዋጭነት ጥናት ከተጠና በኋላ መሆኑንና ከአካባቢው ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው የተለያዩ ምርቶችን ወደ መሐል አገር ለማጓጓዝና ከሌላ አቅጣጫ የመጣ ምርትን ለማሰራጨት እንደሚረዳ፣ የሳይት መሐንዲስ በቋሚነት መኖሩን፣ የጥራት መለኪያ ላብራቶሪ እንዳአለ፣ ውጤቱም ጥሩ መሆኑን፣ የሰው ኃይል/የሠራተኛ ፍልሰት/መቀያየር እንዳለ፣ በቂ ማሽነሪ እንደሌለ፣ የግብዓት አቅርቦት እጥረት መኖሩን ጠቅሰው፤ ለምሳሌ፡-

**በአሁኑ ወቅት የአጣጥ- ማዞሪያ** የአፈር ሥራ (Earth work) ከ97.011 ኪ.ሜ ውስጥ ከ43 ኪ.ሜ (44.33%) ያልተነካ ሲሆን፣ **ለአብነት፡-**

የአፈር ሥራ (Earth work) 25.45%፣ የቤዝ ኮርስ (base course) 21.3 ኪ.ሜ፣ ሰብ ቤዝ (sub base) 26.17 ኪ.ሜ፣ ዋና መሠረት (Major structure) 68.71 ኪ.ሜ፣ አነስተኛ የፍሳሽ ማስወገጃ (Minor Drainage structure) 17.13 ኪ.ሜ፣ አስፓልት (Aspalt) 21.37 ብቻ የተሠራ በመሆኑ፣

የሥራ ተቋራጩ ከፍተኛ የአቅም ችግር እንዳለበት፣ በተደጋጋሚ ሥራ ሲቋረጥ የጊዜ መጓተት፣ ተጨማሪ ወጪ እና የተሰራው መንገድ መበላሸት በዋናነት የተከሰቱ ችግሮች መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

### 1.2 የአጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሌራ የመንገድ ሥራ ተቋራጭ መሐንዲስ የቀረበ ቃለመጠይቅ፡-

በውሉ መሠረት በጊዜ ሰሌዳው እና በተያዘው በጀት ፕሮጀክቱ ስለመጠናቀቁ፣ ካልተጠናቀቀ ለምን እንደማይጠናቀቅ፣ ንዑስ ተቋራጮች እና አቅራቢዎች ስለመኖራቸው፣ በወቅቱ የክፍያ ስለመከፈሉ፣ ፕሮጀክቱን በምን ዓይነት የጨረታ ግዥ እንደተገኘ፣ ፕሮጀክቱ ለብልሹ አሰራር ያለውን ተጋላጭነት ምን ይመስላል የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

የመንገድ ፕሮጀክቱ በጊዜ እንደማይጠናቀቅ፣ ምክንያቱም የዲዛይን ለውጥ፣ የግብዓት (የሲሚንቶ፣ የነዳጅ፣ ወዘተ.) እጥረት እንዳለ፣ የሀገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታ፣ በወቅቱ ክፍያ አለመፈፀም፤ ንዑስ ተቋራጭ እንደሌላቸው፣ **በውድድር የጨረታ ግዥ** እንደተገኘ ገልፀዋል፡፡

### 1.3 ለአጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሌራ የመንገድ ሥራ አማካሪ መሐንዲስ የቀረቡ ቃለመጠይቅ፡-

የዋጭነት (የወጪ ግምት) ጥናት ስለመጠናቱ፣ ሥራው ከመጀመሩ በፊት ውሎችን የመገምገም ሥራ ስለመሰራቱ፣ የሥራ ተቋራጩ በውሉ መሰረት አስፈላጊ መሳሪያዎችን አሟልቶ ስለመግባቱ፣ ፕሮጀክቱ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ያለው ተጋላጭነት፣ በፕሮጀክቱ የሥራ ሂደት ለውጦችና ስጋቶች ሲኖሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት ስለመደረጉ፣ አለመግባባቶች ካሉ የተፈታበት መንገድ፣ ከበጀት፣ ጊዜ እና አገልግሎት አንፃር እንዴት እንደሚታይ፣ ግልፅነትን ተላብሶ ከማከናወን አኳያ ምን እንደሚመስል የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

ውሉን ተዋውለው ከጨረሱ በኋላ የመጡ መሆናቸውን ጠቁመው የዋጭነት (የወጪ ግምት) ጥናት ስለመጠናቱ መረጃው እንደሌላቸው፣ ሥራው ከመጀመሩ በፊት ውሉን እንዳልገመገሙ፣ የሥራ ተቋራጩ መሳሪያዎችን አሟልቶ እንዳልገባ፣ አሁን ላይ ፕሮጀክቱ ለሙስናና ብልሹ አሰራር የተጋለጠ አለመሆኑን፣ ችግሮች ሲኖሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት እንደሚያደርጉ፣ ነገር ግን ከውይይቱ በኋላ የተስማሙባቸው ጉዳዮች ተፈፃሚነት እንደሌላቸው፣ ጊዜው በጣም እንደተጓተተ፤ በመጓተቱ ምክንያት ደግሞ በበጀት ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር፣ ለህብረተሰቡም በወቅቱ አገልግሎት እንደማይሰጥ ምላሽ ሰጠዋል፡፡

### 1.4 ለአካባቢ ነዋሪዎች የቀረበ ቃለመጠይቅ፣

ስለመንገድ ፕሮጀክቱ ያወያያቸው አካል ስለመኖሩ፣ ስለመንገዱ ስለሚሰጠው ጠቀሜታ፣ የነበረው ብልሹ አሰራር ምን እንደሆነ፣ ቅሬታን ለመቀበል የሚያስችል ሥርዓት ስለመዘርጋቱ፣ ለማጠናቀቅ ለምን ረጅም ጊዜ እንደፈጀ፣ ፕሮጀክቱ በተያዘለት በጀት፣ ጊዜ፣ እና ለህብረተሰቡ ከሚሰጠው አገልግሎት አንፃር እንዴት እንደሚመለከቱት እና ግልፅነትን ተላብሶ ከማከናወን አኳያ ያላቸውን ሀሳብ እንዲያቀርቡ ለኗሪዎች ቃለመጠይቅ ቀርቧል፡፡

የቻይናው (**ሻንዶግ ሃይ ዌይ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን**) በሚሰራበት ወቅት ከፍተኛ ብልሹ አሰራር እንደነበር (ቻይናውያን ከሆኑ የኮንትራክተሩ ሠራተኞች ጋር የአካባቢው ሠራተኞች በመመሳጠር የተለያዩ ማቴሪያሎችን (ነዳጅ፣ ብረት፣ወዘተ.) ድልድይ አፍረሶ ብረቱን አውጥቶ እንደሸጡና ሌብነት እንደነበር፣ ቅሬታን ለመቀበል የሚያስችል ሥርዓት እንዳልተዘረጋ፣ ለማጠናቀቅ ረጅም ጊዜ የፈጀውም ሌብነት በመኖሩና በአግባቡና በፍጥነት ባለመሠራቱ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

### 1.5 ለአካባቢው አስተዳደር አካላት የቀረበ ቃለመጠይቅ፡-

2

ምን ያህል  የሥራ ተቋራጭ እና አማካሪዎች እንደተሳተፉ፣ አጠቃላይ በጀቱ ምን ያህል እንደሆነ፣ የተጀመረበትና የሚጠናቀቅበትን ጊዜ መቼ እንደሆነ፣ ከመጀመሩ በፊት ከህብረተሰቡ (ከሚመለከተው አካል) ጋር ስለጠቀሜታው፣ ስለበጀቱ፣ ወዘተ. የተደረገ ውይይት ካለ፣ መንገዱ የሚነካቸው የህብረተሰብ አካላት ካሣ ስለመከፈሉ፤ ካልተከፈለ ለምን፤ የክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማ እና አፈፃፀም ሂደት ምን እንደሚመስል፤ የቀረቡ ጥቆማዎች ምን እንደሆኑ፣ ከተያዘለት በጀት፣ ጊዜ፣ እና አገልግሎት አንፃር እንዴት እንደሚታይ፣ ግልፅነትን ተላብሶ ወይም ከሙስናና ብልሹ አሠራር  ነፃ ሆኖ ከማከናወን አኳያ ያላቸውን አስተያየትና ምላሽ እንዲሰጡ ቃለመጠይቅ ቀርቦላቸዋል፡፡

በፕሮጀክቱ ላይ ሁለት የሥራ ተቋራጮች እና ሁለት አማካሪዎች እንደተሳተፉ፤ አጠቃላይ በጀቱ፣ የተጀመረበትና የሚጠናቀቅበትን ጊዜ እንደሚታወቅ፤ መንገዱ የሚነካቸው የህብረተሰብ አካላት በከፊል ካሣ እንደተከፈለ፤ ቀሪ ክፍያዎች በአዲሱ መመሪያ መሠረት እንደሚከፈል፤ 3 ዞኖችንና ብዙ ወረዳዎችን የሚያገናኝ በመሆኑ ለህብረተሰቡ ከፍተኛ ተጠቀሜታ እንዳለው፤ የአካባቢው ህብረተሰብ ከፍተኛ አምራች ስለሆነ ምርቱን ወደ ማዕከል ለማድረስ፣ ከማዕከል ሸቀጦችን ለማስገባት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው፣ የቀረቡ ጥቆማዎች እንደሌሉ፤ በተያዘለት ጊዜ ሰሌዳ መሰረት እየተሰራ ስላልሆነ ተጨማሪ በጀትና ጊዜ ሊጠይቅ እንደሚችል አብራርተዋል፡፡

## 2. የወራቤ-ቦጆበር የመንገድ ፕሮጀክት፡-







video_2025-05-30_13-34-05.mp4







**ከአካባቢው አስተዳደር አካላት ጋር የተደረገ ውይይት**



## 2.1. በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ለቡታጅራ አካባቢ ግንባታ ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅና ሳይት መሐንዲሶች የቀረቡ ቃለመጠይቅ፡-

የመንገዱ ለምን እንደተመረጠ፤ የአዋጭነት ጥናት ስለመጠናቱ፤ የጥራት መለኪያ ላብራቶሪ ስለመኖሩ፣ የግብዓት አቅርቦት ምን እንደሚመስል፣ አጠቃላይ ሥራው ምን እንደሚመስል፣ የካሳ ክፍያ ስለመጠናቀቁ፤ በቂ ማሽኖች ስለመኖራቸው፣ የግንባታ ግብዓት ማምረቻ ሳይቶች ስለመሟላታቸው፤ ለሥራ ተቋራጮች ምን ያህል ወጪ እንደተደረገ፣ በተደጋጋሚ ሥራ ሲቋረጥ የተከሰተው ችግር ወይም ብልሹ አሠራር ምን እንደነበር፣ ፕሮጀክቱ ከበጀት፣ ጊዜና አገልግሎት አንፃር እንዴት እንደሚታይ፣ ግልጽነትንና ብልሹ አሠራርን ከመከላከል አኳያ ምን ይመስላል የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበው የሚከተሉት ምላሾች ተሰጠዋል፡፡

መንገዱ የተመረጠው ከአካባቢው ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው ምርቶች በተለይም ቅመማ ቅመሞችን ወደ መሐል አገር ለማጓጓዝና ከጅማና ከሌሎች አካባቢዎች የሚመጡ ምርቶችን ለማሰራጨት ከፍተኛ ጠቀሜታ ስላለው፤ የጥራት መለኪያ መኖሩን፣ የአስፓልት ፕላንት ማሽን በመበላሸቱ ለረጅም ጊዜ መቋረጡን፣ የግብዓት አቅርቦት አንፃር የነዳጅ አቅርቦት እጥረት መኖሩን፤ ለምሳሌ የአፈር ሥራ (Earth work) 80% የተሰራ ሲሆን ከ41.35 ኪ.ሜ ውስጥ 20 ኪ.ሜ (48.367%) አስፓልት ለመስራት ቢታቀድም እስካሁን 5 ኪ.ሜ. (25%) ብቻ የተሰራ ስለሆነ በተያዘለት ጊዜ ሰሌዳ መሰረት እንደማይጠናቀቅ፣ የካሳ ክፍያ አብዛኛው የተከፈለ መሆኑንና 190,000,000 ብር ( አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ብር) አካባቢ ያልተከፈለ መሆኑን፣ ከመጀመሪያው ውል ውጪ ከህበረተሰቡ በቀረበው ጥያቄ መሰረት ጥናት በማድረግ 3 ኪ.ሜ ተጨማሪ መንገድ እየተሰራ መሆኑን፣ የግንባታ ግብዓት ማምረቻ ሳይቶች የተሟሉ መሆናቸውን፣ በየወሩ የፕሮጀክቱ ሂደት የሚያሳይ ሪፖርት

እንደሚዘጋጅ፣ ሥራ ተቋራጩ የአቅም ውስንነት እንዳለበት፣ በተደጋጋሚ ሥራ ሲቋረጥ የጊዜ መጓተት፣ ተጨማሪ ወጪ እና የተሰራው መንገድ ብልሽ የሚያጋጥመው መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

### 2.1. ለወራቤ-ቦጀበር የመንገድ ሥራ ተቋራጭ መሐንዲስ የቀረቡ ቃለመጠይቅ፡-

በውሉ ጊዜውና እና በተመደበለት በጀት ስለመጠናቀቁ፣ ካልተጠናቀቀ ለምን እንደማይጠናቀቅ፣ ንዑስ ተቋራጮች እና አቅራቢዎች ስለመኖራቸው፣ በወቅቱ የክፍያ ስለመከፈሉ፣ በምን ዓይነት የጨረታ ግዥ እንደተገኘ፣ ለብልሹ አሰራር ያለውን ተጋላጭነት ምን ይመስላል የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በውሉ መሠረት እንደማይጠናቀቅ፣ ምክንያቱም የወሰን ማስከበር ችግር አለመፈታቱ፣ በኮንትራክተሩ የአቅም ችግር፣ በዋጋ ንረት፣ በማሽነሪ፣ በግብዓት (የሲሚንቶ፣ የነዳጅ፣ ወዘተ.) እጥረት፤ በግልጽ ጨረታ ሳይሆን በቀጥታ ድርድር እንደተገኘ፣ ከገቡ 4 ወር ብቻ ስለሆነ ቅድመ ክፍያውንና እስካሁን የተከፈለውን ክፍያ እንደማያውቁት፣ ያሉት ማሽኖች በሚፈለገው ደረጃ እንደማይሰሩ ገልፀዋል፡፡

### 2.2. ለወራቤ- ቦጀበር የመንገድ ሥራ አማካሪ መሐንዲስ የቀረቡ ቃለመጠይቅ፡-

የዋጭነት(የወጪ ግምት) ጥናት ስለመጠናቱ፣ ሥራው ከመጀመሩ በፊት ውሎችን የመገምገም ሥራ ስለመሰራቱን፣ በምን ዓይነት የጨረታ ግዥ እንደተገኘ፣ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ያለው ተጋላጭነት፣ ከበጀት፣ ጊዜ እና አገልግሎት አንፃር እንዴት እንደሚታይ፣ ግልፅነትን ተላብሶ ከማከናወን አኳያ ምን ይመስላል የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

የዋጭነት(የወጪ ግምት) ጥናት ስለመጠቀቁ መረጃው እንደሌላቸው፣ ሥራው ከመጀመሩ በፊት ውሉን እንደገመገሙት፣ ጨረታው በድርድር እንደገቡ፣ በአሁኑ ወቅት ፕሮጀክቱ ለሙስናና ብልሹ አሰራር የተጋለጠ አለመሆኑን፣ ችግሮች ሲኖሩ ከሚመለከታቸው አካለት ጋር በየወሩ ውይይት እንደሚያደርጉ፣ ተግዳሮቶችን በሚመለከት ደብዳቤ እንደሚጽፉ፣ ነገር ግን ከውይይቱ በኋላ የተስማሙባቸው ጉዳዮች ተፈፃሚነት እንደሌላቸው፣ ጊዜው በመጓተቱ ምክንያት በበጀት ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ምላሽ ሰጠዋል፡፡

### 2.3. ለወራቤ- ቦጀበር አካባቢ ነዋሪዎች የቀረበ ቃለመጠይቅ፣

የነበረው ብልሹ አሰራር ምን እንደሆነ፣ ቅሬታን ለመቀበል የሚያስችል ሥርዓት ስለመዘርጋቱ፣ ለማጠናቀቅ ለምን ረጅም ጊዜ እንደፈጀ፣ የመንገድ ፕሮጀክቱ መጀመሩ በህብረሰበቡ ዘንድ ያመጣው ለውጥ ምን እንደሆነ፣ ፕሮጀክቱ በተያዘለት በጀት፣ ጊዜ እና ለህብረተሰቡ ከሚሰጠው አገልግሎት አንፃር እንዴት እንደሚመለከቱት እና ግልፅነትን ተላብሶ ከማከናወን አኳያ ያላቸውን ሀሳብ እንዲያቀርቡ ለኗሪዎች ቃለመጠይቅ ቀርቧል፡፡

የተጀመረበትን ጊዜ እንደሚያስታውሱ፣ ስለሚቋረጥበት ምክንያት እውቅና እንደሌላቸው፤ ቅሬታን ለመቀበል የሚያስችል ሥርዓት እንደሌለ፣ የካሳ ክፍያው ከ7 ዓመት በላይ በመዘግየቱ አሁን ካለው የገበያ ዋጋ ጋር እንደማይጣጣም፣ ለማጠናቀቅ ረጅም ጊዜ የፈጀው ቀደም ሲል የሰሩት ብልሹ አሰራር ወይም የአሸዋና ጠጠር ሽቀባ/ሌብነት ያካሂዱ ስለነበር፣ በተባለው ጊዜ ስለማይጠናቀቅ ለህብረተሰቡ በፍጥነት አገልግሎት መስጠት የማይችል መሆኑን ኗሪዎች አብራርተዋል፡፡

## 2.4. የወራቤ- ቦጀበር አካባቢ ለአስተዳደር አካላት የቀረበ ቃለመጠይቅ፡-

ምን ያህል የሥራ ተቋራጭ እና አማካሪዎች እንደተሳተፉ፣ አጠቃላይ በጀቱ ምን ያህል እንደሆነ፣ የተጀመረበትና የሚጠናቀቅበትን ጊዜ መቼ እንደሆነ፣ መንገዱ የሚነካቸው የህብረተሰብ አካላት ካሣ ስለመከፈሉ፣ ካልተከፈለ ለምን እንደሆነ፤ የክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማ እና አፈፃፀም ሂደት ምን እንደሚመስል፣ የቀረቡ ጥቆማዎች ካሉ እንዲገለጽ፣ ከተያዘለት በጀት፣ ጊዜ፣ እና አገልግሎት አንፃር አፈፃፀሙ ምን እንደሚመስል፣ ግልፅነትን ተላብሶና ሙስናንና ብልሹ አሠራርን ከመከላከ አኳያ ያላቸውን አስተያየትና ምላሽ እንዲሰጡ ቃለመጠይቅ ቀርቦላቸዋል፡፡

ሶስት የሥራ ተቋራጮች እና ሶስት አማካሪዎች እንደተሳተፉ፤ አጠቃላይ በጀቱ፣ የተጀመረበትና የሚጠናቀቅበትን ጊዜ እንደሚታወቅ፤ መንገዱ የሚነካቸው የህብረተሰብ አካላት በከፊል ካሣ እንደተከፈለ፣ የካሳ ክፍያው በወቅቱ ባለመከፈሉ የተወሰኑ ኗሪዎች በድንኳን እንደሚኖሩ፤ በየጊዜው ክትትልና ድጋፍ እንደሚደረግ፤ የአፈፃፀም ግምገማ እንደሚካሄድ ነገር ግን በሚፈለገው ፍጥነት እየተሰራ እንዳልሆነ፣ 20 ኪ.ሜ አስፓልት እንሰራለን ብለው እስካሁን 5 ኪ.ሜ. ብቻ እንደሰሩ፣ በመሆኑም ተጨማሪ ጊዜና በጀት እንደሚያስከትል፣ ወቅቱን ጠብቆ ለህብረተሰቡ አገልግሎት እንደማይሰጥ ጠቅሰው፣ አሁን ግልፅነትን ተላብሶ እየተከናወነ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

# 5. የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች በርዕሰ ጉዳይ

የመንገድ መሠረተ ልማት ፕሮጀክት ጥናት የግዥ ጨረታና ውል አስተዳደር አሠራር የተከናወነውን ለፌደራል የሥነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 ከተሰጠው ስልጣንና ተግባር በአንቀጽ 7(3) መሰረት በመንግስት መ/ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ለሙስናና ብልሹ አሰራር የተጋለጡ እና ሊጋለጡ የሚችሉ የአሰራር ሥርዓቶችን በማጥናት ወይም እንዲጠኑ በማድረግ የተሰጡ የመፍትሄ /የማሻሻያ/ ሃሳቦችን እንደሚቀርብ፣ ተግባራዊ መሆናቸውን እንደሚከታተል፣ በማይፈፅሙት ላይ ተገቢ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ በህግ የመመርመርና የመክሰስ ስልጣን ላለው አካል እንደሚያቀርብ ተደንግጓል፡፡

በዚህ መሰረት ኮሚሽኑ የፌደራል መንግስት የመንገድ ፕሮጀክቶች የሆኑና በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር አሰሪነት ተጀምረው እየተቋረጡ የሚቀጥሉ የመንገድ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች የግዥ ጨረታና የውል አስተዳደር የአሠራር ሥርዓት ግልጽነት፣ ቁጥጥርና ክትትል፣ የሥራ ተቋራጮች ብቃት ምዘና እና ክትትል አፈፃፀም ክንውን እና ተቋርጠው ለቀጠሉ የመንግስት የመንገድ መሰረተ ልማት ፕሮጀክቶችን ለማጥናት አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ እና በመተንተን በተከናወነው ጥናት መሠረት የሚከተሉት ዋና ዋና ግኝቶች ታይተዋል፡፡

- በ2017 በጀት ዓመት 167 የሚሆኑ ክለሳ ከተደረገባቸው 21 የመንገድ ፕሮጀክቶች ውስጥ 13ቱ ወይም 61.9% የሚሆኑት የመንገድ ፕሮጀክቶች ከ1-7 ዓመት እና በላይ ተጨማሪ ጊዜ የተጠየቀባቸው ሲሆን፣ ፊዚካል አፈፃፀማቸው ከ50% በታች መሆኑ፣
- የ9 የመንገድ ስራ ፕሮጀክቶች በንጽጽር ሲታዩ በመጀመሪያው እቅድ ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 18.172 ቢሊዮን ሲሆን በተከለሰው እቅድ ብር 26.23 ቢሊዮን በላይ ደርሷል፡፡ በዚህ ምክንያት በልዩነት ከብር 8.06 ቢሊዮን በላይ ተጨማሪ ወጪ የተደረገ መሆኑን፣
- ከ21 የመንገድ ስራ ፕሮጀክቶች መካከል በተያዘላቸው በጀትና ጊዜ ያልተጠናቀቁ፣ ተጨማሪ ወጪን የጠየቁ፣ ፕሮጀክቶችን በጊዜው ለማጠናቀቅ የክትትልና የቁጥጥር ክፍተት እንዳለ መረጃዎች የሚያሳዩ መሆኑ፣

## 5.1 የግዥ ጨረታ በሚመለከት

በናሙና በተመረጡ ሁለቱ የመንገድ ፕሮጀክቶች በግልጽ ጨረታ መካሄዱን፣ የግዥ ጨረታ ማስታወቂያ መውጣቱን፣ የጨረታ ሰነድ በመሸጥ አሸናፊዎችንና አማካሪዎች መለየታቸውንና አብዛኛው የወሰን ማስከበር ክፍያ መፈፀሙን በሰነድ መረጃዎች ተረጋግጧል፡፡

**በሌላ በኩል**:-

- የመጀመሪያው ውል በመቋረጡ በተደጋጋሚ ጨረታ መውጣቱ ለተጨማሪ ወጪ፣ የጊዜና የንብረት ብክነት እንዲሁም የተሠራው ሥራ ለብልሽት መዳረጉ፤
- በአጠቃላይ የተቋሙ የመንገድ ግዥ ጨረታ አካሄድ በመጀመሪያው የግዥ እቅድ መሠረት አለመካሄድ፣ የተሟላ ጥናት ሳያካሄዱ ግዥ መፈፀሙን ያመላክታል፡፡ እነዚህ ክፍተቶች ተቋሙ የተመደበለትን በጀት በአግባቡና አስፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች እንዳይጠቀም ከማድረጉ ባሻገር በተደጋጋሚ የግዥ ጨረታ በማካሄድ ከፍተኛ ተጨማሪ ወጪ እንዲያወጣና ጊዜ እንዲባክን አድርጎታል፡፡ የመንግሥትን የግዥ ጨረታ አሠራርን በጥንቃቄንና በጥናት አለመዘርጋት በጨረታ ግዥ ሥርዓቱ ውስጥ ብልሹ አሠራሮች የተከሰቱ መሆኑን ያሳያል፡፡

## 5.2 የውል አስተዳደር በሚመለከት

### 1. የአጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሌራ የመንገድ ፕሮጀክት፡-

- የመጀመሪያው ሥራ ተቋራጭ ሥራውን **በ42 ወራት** ውስጥ አጠናቆ ለማስረከብ ውል መግባቱን፣ አማካሪው ምክር ለመስጠት ውል መፈፀሙን፣ የሥራ ተቋራጩ ደካማ አፈፃፀም ያስመዘገበ በመሆኑ ሥራውን ሳያጠናቅቅ አቋርጦ የወጣ መሆኑን፤
- ለሁለተኛ ጊዜ **በ38 ወራት** ሰርቶ ለማጠናቀቅ ውል መገባቱንና የመንገድ ፕሮጀክቱ **በሰኔ ወር 2017 ዓ.ም** መጨረሻ **34.86 ፊዚካል እና 47% ፋይናንሻል** አፈፃፀም ላይ እንደሚገኝ ከሪፖርት መረጃዎች ለመረዳት የተቻለ መሆኑ፡፡
- በአማራ መንገድ ሥራዎች ሥራ ተቋራጭ መሐንዲስ መግለጫ እስከ ጥር 30 ቀን 2017 ዓ.ም መጨረሻ **54.4%** መድረሱን ቢጠቁሙም ከሪፖርት መረጃው ጋር የማይጣጣም መሆኑ፤
- የመጀመሪያው የሥራ ውል በመቋረጡ ምክንያት **ለሻንዶግ ሃይዌይ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ግሩፕ** ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ ብር **233,059,918.90** (ሁለት መቶ ሰላሳ ሶስት ሚሊዮን አምሳ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ስምንት ከ90/100 ብር) ውስጥ ውሉ ሲቋረጥ መመለስ ያለበት ብር **180,051,945.97** (አንድ መቶ ሰማንያ ሚሊዮን አምሳ አንድ ሺ ዘጠኝ መቶ አርባ አምስት ከ97/100 ብር) ተመላሽ

እንዳልተደረገ እና ውል የተገባው ብር **117,823,523.09** (አንድ መቶ አስራ ሰባት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃያ ሦስት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ሦስት ከ09/100) የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤

- የመጀመሪያው የአማካሪ ውል ብር **20,670,100.00** (ሃያ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰባ ሺህ አንድ መቶ) ሲሆን የመጀመሪያው ውል በመቋረጡ ምክንያት ለሁለተኛው የአማካሪነት ብር **21,552,782.50** (ሃያ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ሰማንያ ሁለት ከ50/100) ተጨማሪ ወጪ መደረጉ፣
- በውሉ መሠረት መጠናቀቅ በሚገባው ዓመት ላይ ውሉ እንዲቋረጥ የተደረገ መሆኑን፣
- የሥራ ተቋራጮችና የአማካሪ ድርጅቶች ውል ሲቋረጥ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፡ ፡
- ለተጨማሪ ወጪ የዳረገው የመንገድ የፕሮጀክት ግንባታ ሥራዎች በተገባላቸው ውል መሰረት አለመጠናቀቃቸው የክትትልና ቁጥጥር ሚናው አነስተኛ መሆኑን እና የተጠናከረ የተጠያቂነት ሥርዓት አለመዘርጋቱን ለሙስናና ብልሹ አሠራር የተጋለጠ መሆኑን ያመላክታል፡ ፡

## 2. የወራቤ-ቦጆበር የመንገድ ፕሮጀክት፡ -

- የመጀመሪያው ውል ከአሸናፊው ሥራ ተቋራጭ ጋር በብር **458,445,650.00** (አራት መቶ ሃምሳ ስምንት ሚሊዮን አራት መቶ አርባ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ) የተዋዋለ ቢሆንም በውሉ መቋረጥ ምክንያት ለሁለተኛው ውል በብር **795,000,000** (ሰባት መቶ ዘጠና አምስት ሚሊዮን) በተጨማሪ የተዋዋለ ሲሆን፣ የሁለተኛው ውል በመቋረጡ ምክንያት ደግሞ ለሦስተኛው ውል በብር **2,777,252,940.36** (በሁለት ቢሊዮን ሰባት መቶ ሰባ ሰባት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ ከ36/100) በተጨማሪ የተዋዋለ መሆኑ፣
- የመጀመሪያው አማካሪ በብር **19,965,211.85** (በአስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ስልሳ አምሰት ሺህ ሁለት መቶ አስራ አንድ ከ85/100) ውል የተፈፀመ ሲሆን ውሉ ሲቋረጥ ከሁለተኛው አሸናፊ አማካሪ ጋር በብር **18,451,520.00** (አስራ ስምንት ሚሊዮን አራት መቶ አምሳ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሃያ) ተጨማሪ የሥራ ውል የተፈራረመ መሆኑን፣ እንዲሁም ሁለተኛው አሸናፊ አማካሪ ሲቋረጥ ከሦስተኛው አማካሪ ጋር በብር **12,401,743.75** (አስራ ሁለት ሚሊዮን አራት መቶ አንድ ሺህ ሰባት መቶ አርባ ሦስት ከ75/100) ተጨማሪ የሥራ ውል የተዋዋለ መሆኑ፣

- የመጀመሪያውና ሁለተኛው የሥራ ውል በመቋረጡ ምክንያት **በልዩነቱ ብር 2,318,807,290.36** (ሁለት ቢሊዮን ሦስት መቶ አስራ ስምንት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና 36/100) ተጨማሪ ወጪ የወጣ መሆኑ፤
- ለማርካን ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማህበር ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ ብር 159,000,000.00 (አንድ መቶ አምሳ ዘጠኝ ሚሊዮን ብር) ውስጥ ብር 79,500,000.00 (ሰባ ዘጠኝ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ) ለመንግስት ተመላሽ እንዳልተደረገና ውል የተገባው የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ውሎቹ ከተቋረጡ በኋላ በድጋሚ ውል ሳይዋዋሉ ለረጅም ጊዜ መቆየቱ የተሠራው ሥራ ለብልሽት የሚያጋልጥና ለተጨማሪ ወጪ የተዳረገ መሆኑ፤
- የወራቤ-ቦጆበር የመንገድ ፕሮጀክት **የአዋጭነት ጥናት** ያልተጠና መሆኑ፤

- ሶስተኛው የወራቤ-ቦጆበር መንገድ ፕሮጀክት ያለጨረታ በቀጥታ በውሳኔ የተሰጠ መሆኑ፣
- የመጀመሪያውና ሁለተኛው ውል በመቋረጡ በተደጋጋሚ ጨረታ መውጣቱ ለተጨማሪ ወጪ፣ የጊዜና የንብረት ብክነት እንዲሁም የተሠራው ሥራ ለብልሽት መዳረጉ፤

## 5.3 ቃለ-መጠይቅ በሚመለከት

### 5.3.1 የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር፡-

- የተቋራጭ የአቅም ውስንነት፣ የግብዓት አቅርቦት እጥረት፣ የክፍያ መዘግየት፣ የዋጋ ግሽበት ዝቅተኛ አፈፃፀም እንዲኖራቸውና ለረጅም ጊዜ እንዲዘገዩ ያደረጋቸው መሆኑ፣
- የአማካሪዎችን የጨረታ ውድድር በተመለከተ በ “Shortlist“ የተሻለ አቅምና ብቃት ያላቸው በሚል የሚመረጡ መሆኑ፣

### 5.3.2 ከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር፡-

- በየኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የታቀደውን እቅድ በመገምገም የጋራ እቅድ አድርገው የሚሰሩ መሆኑ፣
- በቋሚነት የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ክትትልና ድጋፍ የሚያደርጉ መሆኑ፣
- የሀገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች ከፍተኛ የአቅም ውስንነት ያለባቸው በሚል ብዙ ጊዜ በጨረታው የማይመረጡ መሆናቸው፣

### 5.3.3 የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን፡-

- የዲዛይን፣ የጨረታ፣ የኮንትራት ይዘትና በውል አስተዳደር እንዲሁም በግንባታ ጥራት እና ቁጥጥር ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው የአሠራር ሥርዓት አለመዘርጋቱን፣ አፈፃፀሙን አለመከታተሉን፣ ያላረጋገጠና ያልተቆጣጠረ መሆኑ፤
- በጨረታና ውል መሰረት በዲዛይን፣ በዋጋ፣ በጥራትና በጊዜ ተሰርተው ስለመጠናቀቃቸው እና ርክክብ ስለመደረጉ ያልተከታተለ፣ ያልተቆጣጠረ፣ የእርምት እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ፤
- የዋጋ ግምቶች በአግባቡ ስለመዘጋጀታቸው ያልተቆጣጠረ፣ ያላረጋገጠ መሆኑ፣
- መሥራት ለሚችሉ የመንገድ ሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና በዘርፉ የሚሳተፉ ሌሎች ድርጅቶችን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በደንብ ለይቶ ያልሰጠ፣ ያልተቆጣጠረ፣ ያላገደ፣ ያልሰረዘ፣ ወይም ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያላደረገ መሆኑ፤

## 5.4 ኦዲትን በሚመለከት

### 5.4.1 የተቋሙ የውስጥ ኦዲት፡-

- በየጊዜው ኦዲት እንደሚደረግ መረጃዎች የሚያሳዩ መሆናቸው፣
- የግዥ አፈጻጸም መመሪያው ግዥ ሲፈጽሙ በውድድሩ ተሳታፊ የሚሆኑት አቅራቢዎች እስከተቻለ ድረስ ቁጥራቸው ከሶስት ማነስ እንደሌለበት ቢገልጽም የመ/ቤቱ የ2016 ዓ.ም 4ኛ ሩብ ዓመት የውስጥ ኦዲት ሪፖርት በመንገድ ፕሮጀክት የግዥ አፈፃፀም የአሰራር ግድፈት የተለመደና በተደጋጋሚ የሚታይ የግዥ መመሪያ ጥሰት ከመሆኑም ባለፈ ለብልሹ አሰራር መንገድ የከፈተ መሆኑ፣

### 5.4.2 የፌደራል ዋናው ኦዲተር፡-

- የፌደራል መንገዶች አስተዳደር ያካሄደው የ2015 የኦዲት ሪፖርት እንደሚያመላክተው በናሙና ከታዩ 10 የተቋረጡ የመንገድ ፕሮጀክቶች ውስጥ የ9 ፕሮጀክቶች በድምሩ ብር **1,301,857,648.25** (አንድ ቢሊዮን ሶስት መቶ አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺ ስድስት መቶ አርባ ስምንት ከ25/100) ለመንግስት ገቢ አለመደረጉ፣
- ለተቋራጮች የተከፈለ የቅድመ ክፍያ እና የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤

- በናሙና ከታዩ 10 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ ተመልሰው ወደ ግንባታ የገቡ 4 የመንገድ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ ባለመደረጉ በድጋሚ ከሌላ ኮንትራክተር ጋር በተደረገ ውለታ ከፍተኛ የገንዘብ **ልዩነት ብር 8,488,441,474.56** (ስምንት ቢሊዮን አራት መቶ ሰማንያ ስምንት ሚሊዮን አራት መቶ አርባ አንድ ሺህ አራት መቶ ሰባ አራት ከ56/100) መረጃው የሚያሳይ መሆኑ፤
- የ2016 ዋናው ኦዲተር ሪፖርት በናሙና ካያቸው 296 የመንገድ ፕሮጀክቶች ውስጥ 4 ዓመትና ከዚያ በላይ የዘገዩ እና ከዚህ ውስጥ 127 ፕሮጀክቶቹ ያሉበትን ደረጃ የሚያሳይ መረጃ ያልተገኘላቸው እና ከ267 ቢሊዮን ብር በላይ ተጨማሪ በጀት የጠየቁ መሆኑ፣
- በእቅድ ከተያዘ በጀት ብር 13.2 ቢሊዮን በላይ ተጨማሪ በጀት የወጣባቸው ከ180 በላይ የመንገድ ፕሮጀክቶች መኖራቸው፤ ከዚህ ውስጥ ከ75 በመቶ በላይ ተጨማሪ ወጪ የወጣላቸው የመንገድ ፕሮጀክቶች መኖራቸው፣

## 5.5 የመስክ ምልከታ

- **መስክ ምልከታ** በውሉ መሰረት በቂ መሳሪያዎች/ማሽነሪዎች ተሟልተው ባለመቅረባቸው፣ ያሉትም ቢሆን በብልሽት ለረጅም ጊዜ በመቆየታቸው እና በቂ ክትትልና ቁጥጥር ባለመደረጉ በፕሮጀክቱ ላይ ከፍተኛ የገንዘብና የጊዜ ብክነት ከማስከቱ ባሻገር ለሙስናና ብልሹ አሠራር የተጋለጠ መሆኑ፤ **ለአብነት፡-**
- የአፈር ሥራ (Earth work) 25.45%፣ የቤዝ ኮርስ (base course) 21.3 ኪ.ሜ፣ ሰብ ቤዝ (sub base) 26.17 ኪ.ሜ፣
- ዋና መሠረት (Major structure) 68.71 ኪ.ሜ፣ አነስተኛ የፍሳሽ ማስወገጃ (Minor Drainage structure) 17.13 ኪ.ሜ፣ አስፓልት (Aspalt) 21.37 ኪ.ሜ ብቻ የተሠራ ሲሆን በውሉ መሠረት የማይጠናቀቅ መሆኑ፣
- የወራቤ-ቦጆበር ሶስተኛው ሥራ ተቋራጭ ፕሮጀክቱን በጨረታ ግዥ ውድድር ሳይሆን በቀጥታ ድርድር የተገኘ መሆኑ፣ ለምሳሌ፡-
- የአፈር ሥራ (Earth work) 80% የተሰራ ሲሆን፣ ከ41.35 ኪ.ሜ ውስጥ 20 ኪ.ሜ (48.367%) አስፓልት ለመስራት ቢያቅዱም እስካሁን 5 ኪ.ሜ. (25%) ብቻ የተሰራ ሲሆን፣ በተያዘለት ጊዜ ሰሌዳ መሰረት እየተሰራ ስላልሆነ ተጨማሪ ወጪና ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑ፣
- የካሳ ክፍያ ከ7 ዓመት በላይ በመዘግየቱ አሁን ካለው የገብያ ዋጋ ጋር የማይጣጣም ስለሆነ የአካባቢው ነሪዎችን ለቅሬታና ለኪሳራ የዳረጋቸው መሆኑ፣

- በመጨረሻ በተያዘው ውል **የአጣጥ-ማዞሪያ** የመንገድ ፕሮጀክት **የካቲት 2018** ዓ.ም ለማጠናቀቅ ውል የተፈፀመ ቢሆንም ተጨማሪ **ሁለት ዓመት** የሚሆን ጊዜ እንደሚያስፈልገው፤ እንዲሁም፡-
- ወራቤ-ቦጆበር የመንገድ ፕሮጀክት ደግሞ መስከረም 2018 ዓ.ም ለማጠናቀቅ ውል የተያዘ ቢሆንም ተጨማሪ **ከዘጠኝ ወራት** በላይ ጊዜ የሚያስፈልገው መሆኑ፤
- በአጠቃላይ ሁለቱ የመንገድ ፕሮጀክቶች እ.ኤ.አ ከግንቦት 06/2017 እና እ.ኤ.አ ከህዳር 19/2015 ጨረታ ወጥቶ ተዋውለው ወደ ሥራ የገቡ ቢሆንም ለ10 ዓመትና በላይ በመቆየታቸው ከፍተኛ የጊዜና የሀብት ብክነት ያስከተሉ መሆናቸውን በቃለ-መጠይቅ፣ በሰነዶችና በመስክ ምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 6. የጥናቱ ምክረ-ሐሳብ፣

ከላይ የተጠቀሱትን የጥናት ግኝቶች ለማሻሻል የሚረዱ ምክረ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 6.1 የፌደራል መንገዶች አስተዳደር፡-

- በአንድ መንገድ ላይ በተደጋጋሚ የግዥ ጨረታ የሚካሄድ ስለሆነ ይህንን ለማስቀረት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በመሥራትና የተሟላ ጥናት በማካሄድ ያሉ ብልሹ አሠራሮችና ክፍተቶችን በመሙላት ለተቋሙ የተመደበውን በጀት ለተመደበለት ዓላማ ቢውል፤
- የግዥ አፈፃፀም መመሪያን መጣስ ለብልሹ አሰራር መንገድ የሚከፍት ከመሆኑም ባሻገር በህግ የሚያስጠይቅ ስለሆነ የመንግስትን የግዥ አፈፃፀም መመሪያን መሠረት ያደረገ ግዥ ቢፈፀም፤
- ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በመንግስት በጀት እንዲገነቡ ውል የተያዘላቸውን የመንገድ መሰረተ ልማት ፕሮጀክቶችን አጠቃላይ መረጃ በመያዝ በፕሮጀክቶች መቋረጥ እየደረሰ ያለውን ከፍተኛ ተጨማሪ ወጪ፣ ሙስና (የገንዘብና የንብረት ብክነት) እና የአገልግሎት አቅርቦት ችግር ከመሰረቱ ሊፈታ የሚያስችል አሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ኃላፊነታቸውን የማይወጡ ሥራ ተቋራጮች ላይ የእርምት እርምጃ የሚወሰወድበት አሰራር ተግባራዊ ቢደረግ፤
- ለመንገድ ፕሮጀክቶች መልካም አፈፃፀም ሲባል የመንግስትን የመንገድ ፕሮጀክቶች የሚሰሩ ተቋራጮች አስቀድመው በወሰዱት ውል መሰረት የመንገድ ፕሮጀክት ላይ ያሳዩት አፈፃፀም በቀጣይ የሚወዳደሩበት ፕሮጀክት ለማሸነፍ እንደመስፈርት እንዲገባ በማድረግ ተቋራጮችን የያዙትን ፕሮጀክት ጊዜውንና

ጥራቱን ጠብቀው በኃላፊነት መሥራት ለቀጣይ ሥራዎች ዋስትና መሆኑን እንዲገነዘቡ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ሊዘረጋ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ቢዘጋጅ፤

- የመንገድ ሥራዎቹ ውለታቸው ተቋርጦ ረጅም ጊዜ አስቆጥረው ለዘላቂ የጥራት ችግርና ለድጋሚ ጥገና እየተጋለጡ ስለሆነ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይቶችን በማድረግ በአጭር ጊዜ ውስጥ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ቢያስቀምጥ፤
- በገቡት ውል መሰረት ግዴታቸውን ሳይወጡ የመንገድ ፕሮጀክቶችን አቋርጠው ከሄዱ ሥራ ተቋራጮች ለመንግስት ገቢ መደረግ የነበረበት የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በወቅቱ ገቢ እንዲደረግ ከመንገድ ፕሮጀክት ባለቤቶች እና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ጠንካራ የክትትል ሥራ ቢሠራ፤
- ጠንካራ ክትትል በማድረግ ለተቋረጡ የመንገድ ፕሮጀክቶች የተከፈለው የቅድመ ክፍያ ተመላሽ ሆኖ ለሌሎች የልማት ሥራዎች እንዲውል ቢደረግ፤
- በደንብ ቁጥር 247/2003 በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት በመንግስትም ሆነ በግል ድርጅቶች የሚሰሩ የመንገድ ስራዎች ሲሰሩ በአካባቢው ህብረተሰብ ላይ ጉዳት ለመከላከል የሚያስችል ጠንካራ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ ኃላፊነቱን ቢወጣ፤
- የሥራ ውሎች ሲቋረጡ የአማካሪ ውሎችም ተጨማሪ ወጪ ከመደረጉ በፊት ቢቋረጥ፤
- ደካማ አፈፃፀም ወይም በሌላ ምክንያት ሥራ ሲቆም ረጅም ጊዜ ሳይወስድ ወዲያኑ ውሉን ማቋረጥ ቢቻል፤ ደካማ አፈፃፀም ያስመዘገበ እና ሥራውን ሳያጠናቅቅ አቋርጦ የወጣ ሥራ ተቋራጭ ላይ ወቅታዊ የእርምት እርምጃ ቢወሰድ፤
- የመንገድ የፕሮጀክት ግንባታ ሥራዎች በተገባላቸው ውል አለመጠናቀቃቸው የክትትልና ቁጥጥር ሚናው አነስተኛ መሆኑን እና የተጠናከረ የግልጽነትና  የተጠያቂነት ሥርዓት አለመዘርጋቱን ስለሚያመላክት ይህ ቢሻሻል፤
- የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር እና የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ፊዚካል እና ፋይናንሻል አፈፃፀም መረጃዎች የማይመሳሰሉ በመሆናቸው ተናበና ተቀናጅቶ ቢሰራ፣
- ውሎቹ ከተቋረጡ በኋላ ጨረታ አውጥቶ በድጋሚ ውል ለመዋዋል ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ ስለሆነ ይህን በማሳጠር  የገንዘብ፣ የጊዜና የጉልበት ብክነት መቀነስ ቢቻል፣
- በመንገድ ሥራ ተቋራጭነት ዘርፍ ፈቃድ ወስደው እየተንቀሳቀሱ ለሚገኙ የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች በተቀመጠው መመሪያ መሰረት የብቃት ማረጋገጫ በመስጠት/እንዲሰጥ በማድረግ በሌሎች የሀገሪቱ ህጎች

ላይ ለውጭ አገር ድርጅቶች የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎችን በተመለከተ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት (ከፌደራል ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን) ጋር በቅንጅት በመስራት ጠንካራ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ ሙስናን መከላከል ቢቻል፤

- በመንገድ የስራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ እና ደረጃቸውን ለማሳደግ የሚመጡ ሥራ ተቋራጮች በሰነድ የሚያቀርቧቸው መሳሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎችና የሰው ኃይል በአካል መኖራቸውን የሚያረጋግጥበት፣ ከተሰጣቸው ደረጃ ውጭ የሚሰሩ የሥራ ተቋራጮች እንዳይኖሩ፣ እንዲሁም የብቃት ማረጋገጫቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የስራ ተቋራጮችን በቅድሚያ ሙስና ለመከላከል የሚያስችል፤ ወደ ህገ ወጥ ሥራ ገብተው ሲገኙም እርምጃ የሚወሰድበት የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ቢደረግ፤
- የፌደራል መንገዶች አስተዳደርና የሚመለከታቸው አካላት እድሳት ለማድረግ የሚመጡ ሥራ ተቋራጮች በሰነድ የሚያቀርቧቸው ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች እንዲሁም የሰው ኃይል በአካል መኖራቸው በክትትልና ቁጥጥር ሪፖርት ከተረጋገጠ በኋላ እድሳት ቢደረግ፤
- በፌደራል፣ በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች ያለው በየደረጃው የሚከናወነው የስራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ፣ የቁጥጥር እና የምዝገባ ሥራ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ በሆነ መልኩ ለመምራት የሚያስችል ተመሳሳይ ስታንዳርድ በማዘጋጀት ወጥ በሆነ መልኩ እንዲጠቀሙበት ማድረግ ቢቻል፤
- የመንገድ ፕሮጀክቶችን አጠቃላይ መረጃ እንደ ሀገር መዝግቦ በመያዝ ክትትል ለማድረግ የሚያስችል የፌደራሉን እና የክልሎችን/የከተማ አስተዳደሮች ሚና የለየ፣ የሥራ ተቋራጮችን መብትና ግዴታ በግልፅ ያስቀመጠ አስገዳጅ የፕሮጀክት ምዝገባ መመሪያ በማዘጋጀት እና ተግባራዊ በማድረግ አሁን እየታየ ያለውን የፕሮጀክቶች የአፈፃፀም ክፍተት፣ ሙስናና ብልሹ አሰራር እንዲሁም እንደሀገር ያለውን የተደራጀ የመረጃ እጥረት እንዲቀረፍ ቢደረግ፤
- የፌደራል መንገዶች አስተዳደር በፌዴራል መንግስት በጀት የመንገድ ፕሮጀክቶች ያሉበትን ወቅታዊ መረጃ በመያዝ ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የመንግስትን ከፍተኛ ተጨማሪ የገንዘብ ወጪና ብክነት ከሙስና እና ብልሹ አሠራር በመታደግ ተጠቃሚዎችን ከፕሮጀክቶቹ ወቅታዊ አገልግሎት እንዲያገኙ ቢደረግ፤
- የፌደራል መንገዶች አስተዳደር የመንገዶችን አጠቃላይ መረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አንድ ወጥ የመረጃ ቋት (data base) አደራጅቶ በመያዝ ራሱም ሆነ ሌሎች የመረጃው ተጠቃሚ አካላት እንዲጠቀሙበት በማድረግ፣ በሀርድ ኮፒ ያሉትን ወደ ሶፍት ኮፒ ቀይሮ በመያዝ እና በሀርድ ኮፒ ያሉትንም ከብልሽት እንዲጠበቁ ቢደረግ፤

- የፌደራል መንገዶች አስተዳደር ከባለድርሻ አካላት ጋር ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ትስስር እና ጠንካራ ግንኙነት በማድረግ በጋራ ሊፈቱ የሚችሉ የሙስናና ብልሹ አሠራር ችግሮችን ቢቀርፍ፤
- የተቋራጭ የአቅም ውስንነት፣ የግብዓት አቅርቦት እጥረት፣ የክፍያ መዘግየት፣ የዋጋ ግሽበት ዝቅተኛ አፈፃፀም እንዲኖራቸውና ለረጅም ጊዜ እንዲዘገዩ የሚያደርጋቸው ስለሆነ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በመሥራት የተዘረዘሩ ችግሮችን ፈጥኖ መፍታት ቢቻል፤
- የሀገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች ከፍተኛ የአቅም ውስንነት ያለባቸው ስለሆነ ከውጪ ሀገር ተጫራቾች ጋር ተወዳድረው እንዲያሸንፉ የሚመለከታቸው (ከተማና መሠረተ ልማት ሚንስቴር፣ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር) በመተባበር የአቅም ግንባታ ድጋፍ ቢደረግ፣
- የተቋሙ የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ማስተባበሪያ የሥራ ክፍል (መከታተያ ክፍል) የአቅም ውስንነት በማጠናከር፣ በማብቃትና በመደገፍ ሙስናና ብልሹ አሠራርን በተጠናከረ መልኩ እንዲከላከሉ ቢደረግ፣

## 6.2 በተጨማሪ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሠረት በመንገድ ፕሮጀክቶች፡-

- የዲዛይን፣ የጨረታ፣ የኮንትራት ይዘትና በውል አስተዳደር እንዲሁም በግንባታ ጥራት እና ቁጥጥር ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው የአሠራር ሥርዓት ቢዘረጋ፣ አፈፃፀሙን ቢተከታተል፣ ቢያረጋግጥና ቢቆጣጠር፤
- በጨረታና ውል መሰረት የዋጋ ግምቶች በአግባቡ ስለመዘጋጀታቸው፣ በጥራትና በጊዜ ተሰርተው ስለመጠናቀቃቸው እና ርክክብ ስለመደረጉ ቢተከታተል፣ ቢቆጣጠር፤ የእርምት እርምጃ ቢወስድ፣
- የመንገድ ሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና በዘርፉ የሚሳተፉ ሌሎች ድርጅቶችን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በደንብ ለይቶ ቢሰጥ ቢቆጣጠር፣ ቢያግድ፣ ቢሰርዝ፣ ወይም ህጋዊ እርምጃ ቢወስድ፤
- በመንገድ ሥራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ ሲሰጥና ደረጃ ሲያሳድጉ በየደረጃው በአነስተኛ መስፈርትነት የተቀመጠውን የማሽነሪና የተሽከርካሪ፣ የሰው ኃይል፣ ዓመታዊ ተርንኦቨር፣ ወዘተ. ያሟሉ መሆኑን፣ ከሌሎች የመንግስትና የግል ተቋማት የሚቀርቡ የሰነድ ማስረጃዎች ትክክለኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እና የታዩ ክፍተቶችን ለማረም የሚረዳ የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተግባራዊ ቢደረግ፤

## 7. የጥናቱ ምክረ-ሐሳብ ክትትልና ድጋፍ ስልቶች፣

በዚህ ጥናት ከተገኘው አጠቃላይ ውጤት እና መደምደሚያ አንፃር የፌዴራል መንገዶች አስተዳደር የጨረታ ግዥና የውል አስተዳደር አሰራር ላይ የተጠቀሱትን የጥናት ግኝቶች ለማሻሻል፤ ግልፅነትና ተጠያቂነት ያጋጠሙትን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ የሚረዱ ምክረ ሀሳቦችን መሠረት ያደረግ እንደሚከተለው የክትትልና ድጋፍ ስልቶች ይቀየሳል፡-

- የጥናቱ ምክረ-ሐሳብ ማስፈፀም የሚያስችል የድርጊት መርሃ ግብር ማውጣት፣
- በእቅድ መሠረት ለአንድ መንገድ የጨረታ ግዥና ውል ከመገባቱ በፊት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በማጠናቀቅ ተደጋጋሚ የጨረታ ግዥና ውል በማስቀረት የመንግስትን ተጨማሪ ወጪ ማስቀረት እንዲችሉ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- የመንግስትን ግዥ አፈፃፀም መመሪያን መሠረት ያደረገ ግዥ እንዲፈጽሙና ለብልሹ አሰራር መንገድ የሚከፍቱ አሠራሮች እንዲወገዱ ክትትል ማድረግ፤
- የሥራ ተቋራጭ የአቅም ውስንነት እንዲቀረፍ በሚመለከተው አካል የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና እንዲሰጥ ድጋፍ ማድረግ፤
- በፕሮጀክቶች መቋረጥ እየደረሰ ያለውን ተጨማሪ ወጪ፣ የገንዘብና የንብረት ብክነት እና የአገልግሎት አቅርቦት ችግር ከመሰረቱ ለመፍታት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ማድረግ፤
- የመንገድ ፕሮጀክቶችን የሚሰሩ ተቋራጮች አስቀድመው በወሰዱት ውል መሰረት የመንገድ ፕሮጀክት ላይ ያሳዩት አፈፃፀም በቀጣይ የሚወዳደሩበት ፕሮጀክት ለማሸነፍ እንደመስፈርት እንዲገባ ለማድረግ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ እንዲዘጋጅ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ክትትል ማድረግ፤
- የመንገድ ፕሮጀክቶችን አቋርጠው ከሄዱ ሥራ ተቋራጮች ለመንግስት ገቢ መደረግ የነበረበት የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በወቅቱ ገቢ እንዲደረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ክትትል ማድረግ፤
- መንገዶች ሲሰሩ በአካባቢው ህብረተሰብ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የመስክ ምልከታ ማድረግ፤
- የሥራ ተቋራጭ ውሎች ሲቋረጡ የአማካሪ ውሎችም ተጨማሪ ወጪ ከመደረጉ በፊት እንዲቋረጡ ክትትልና ድጋፍ ማካሄድ፤
- የመንገድ የፕሮጀክት ግንባታ ሥራዎች በተገባላቸው ውል መሰረት በዲዛይን፣ በዋጋ፣ በጥራትና በጊዜ ተሰርተው እንዲጠናቀቁ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

- ውሎቹ ከተቋረጡ በኋላ ጨረታ አውጥቶ በድጋሚ ውል ለመዋዋል ጊዜውን በማሳጠር የገንዘብ፣ የጊዜና የጉልበት ብክነት እንዲቀንስ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- በመመሪያው በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት/እንዲሰጥ ለማድረግ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት በተለይ ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ጋር በቅንጅት ጠንካራ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ፤
- የሥራ ተቋራጮች በሰነድ የሚያቀርቧቸው መሳሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎችና የሰው ኃይል በአካል መኖራቸውንና በተሰጣቸው ደረጃ የሚሰሩ መሆናቸውን በመስክ ምልከታ ማረጋገጥ፣ በህገ ወጥ ሥራ ገብተው ሲገኙም ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት እንዲዘረግ ድጋፍ ማድረግ፤
- የሥራ ተቋራጮችን መብትና ግዴታ በግልፅ ያስቀመጠ አስገዳጅ የፕሮጀክት ምዝገባ መመሪያ እንዲዘጋጅ እና ተግባራዊ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- የመንገዶችን አጠቃላይ መረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አንድ ወጥ የመረጃ ቋት (data base) እንዲደራጅ ድጋፍ ማድረግ፤
- የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ከባለድርሻ አካላት ጋር ዘመናዊ የቴክኖሎጅ ትስስር እና ጠንካራ ግንኙነት በማድረግ በጋራ ሊፈቱ የሚችሉ የሙስናና ብልሹ አሠራር ችግሮችን ለመቅረፍ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር እና የሚመለከታቸው አካላት በቅንጅት እንዲሰሩ የትስስርና የትብብር ሥራ መሠራት፤
- የመንገድ ሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በደንብ ተጣርቶ እንዲሰጥ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤

# 8. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች፣

## 8.1 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

- የትራንስፖርት እና የመሰረታዊ ቁሳቁሶች (የስልክ፣ የማስታወሻ፣ እስክርቢቶ፣ ወረቀት፣ ወዘተ.) እጥረት መኖር፤
- ተቋሙ ላይ መረጃዎችን በሚፈለገው የጊዜ ገደብ ማግኘት አለመቻል፤
- ተቋሙ ለመረጃ ፈላጊዎች፣ ለአጥኚዎችና ለተመራማሪዎች የሚሆን አንድ የመረጃ ቋት አለመኖር፤

- በፌደራል የሥራ ቋንቋ በአማርኛ ምንም ዓይነት የጨረታ ግዥና የውል ስምምነት ሰነድ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤

## 8.2 በጥናቱ ወቅት የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች፣

- በግል ወጪ ለመሸፈን ጥረት ተደርጓል፤
- በተደጋጋሚ በመሄድ መረጃዎችን ለማግኘት ተችሏል፤
- በመተርጎም፣ የተለያዩ መንገዶች እና ቴክኖሎጂን በመጠቀም ለመረዳት ተሞክሯል፤

## ማጠቃለያ

ዘርፉ መንግስት ከፍተኛ በጀት ከሚመድብባቸው አንዱ በመሆኑ ይህንኑ ሀብት ውጤታማ በሆነ መልኩ በወጪ፣ በጊዜ፣ በጥራት እና ለተፈለገው ዓላማ ማዋል ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አኳያ በዚህ ጥናት የፌደራል መንግስት የሚያካሄዳቸውን የመንገድ ፕሮጀክቶች ጥናት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የግዥ ዕቅድ ዝግጅት፣ የጨረታ ሰነድ ዝግጅት፣ የጨረታ ግዥ  የጥሪ ማስታወቂያ፣ የጨረታ ግዥ የውድድር ሂደት፣ የጨረታ ሰነድ ግምገማ፣ የውል አስተዳደር ክትትልና ቁጥጥር አሠራር፣ ድህረ ውል፣ እንደገና የውል መዋዋልና የውል መቋረጥ፣ በግዥ በውል ዙሪያ ለግልጽነት መጓደል ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የአሠራር ክፍተቶችን በጥናት ለመለየት ጥረት ተደርጓል፡፡

በፌዴራል መንገዶች አስተዳደር የጨረታ ግዥ እና የውል አስተዳደር ሂደት ላይ የሚደረግ የክትትልና የቁጥጥር አሠራር የተጠናከረ ባለመሆኑ የግዥ ህጉ የሚሸራረፍበት ሁኔታ እንደሚስተዋል ለጥናቱ ከተሰበሰቡ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡

የጨረታ ግዥ በተያዘለት እቅድ መሠረት ጊዜውን ጠብቆ የማይሠራ ስለሆነ ተደጋጋሚ ጨረታ እየወጣ በተያዘለት ጊዜ ለመፈጸም እንቅፋት እንደሚሆን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የመንገድ ፕሮጀክቶች ውል በተደጋጋሚ እየተቋረጠ የመንግስትና የህዝብ ሀብት ለአላስፈላጊ ወይም ለተጨማሪ ወጪ የተዳረገ መሆኑን ከተገኙ መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡

በመጨረሻም በግዥ ሂደትና በውል አስተዳደር ግልጽነትና ተጠያቂነት በማጎልበት ውጤታማ የግዥ አፈፃፀም እና የውል አስተዳደር በመከተል በዚህ ጥናት የተለዩ የአሠራር ክፍተቶችን ለመቅረፍ ተጨማሪ ጥረት ቢያደርጉ በግዥ አፈፃፀም ሂደትና በውል አስተዳደር እየተስተዋሉ የሚገኙ ብልሹ አሠራሮች ከመቅረፍና ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር እንዲዘረጋ የሚያስችል ይሆናል፡፡

# አባሪዎች

## አባሪ 1

**ሠንጠረዥ 1፡- የመጀመሪያ ጨረታ ሂደት**

| ተ.ቁ | የፕሮጀክት ስም | ፕሮጀክቱ መገኛ | ርዝመት | የጨረታው አይነት | የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ስለማሲያዝ | ለሥራ ተቋራጭ ጨረታ የወጣበት ቀንና የጨረታ ቁጥር | ጨረታውን የገዙ ብዛት | ጨረታውን ሞልተው የመለሱ ብዛት | ጨረታው የተከፈተበት ቀን | ለቴክኒክና ፋይናንሻል ያለፉ ብዛት | አማካሪ ጨረታ የወጣበት ቀን እና የጨረታ ቁጥር | የአዋጭነት ጥናት ስለመካሄዱ | የወሰን ማስከበር ስራ አፈፃፀም (ከውል በፊት ስለመከናወኑ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አጣጥ ማዞሪያ - ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሴራ | ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | 97 ኪ.ሜ | ግልጽ | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 5,080,768.22$ | እ.ኤ.አ የካቲት 20 እና 21/ 2017 W/44/ICB/OC/GOE/2009 EFY | 22 | 6 | እ.ኤ.አ ግንቦት 06/2017 | 4 | S/73/NCB/RP/GOE/2009/EFY እ.ኤ.አ የካቲት 02 እና 03/2017 | ተካሂዷል | ሠንጠረዥ 2 ላይ ተመላክቷል |
| 2. | ወራቤ-ቦጀበር | ማዕከላዊ ሪጅን (ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል) | 38.5 ኪ.ሜ | ግልጽ | አፍሪካ ኢንሹራንስ 45,344,565.00 | እ.ኤ.አ ግንቦት 15/2015፣ W/33/NCB/OC/GOE/2007 EFY | 35 | 16 | እ.ኤ.አ ህዳር 19, 2015 8:30 ሰዓት | ቴክኒካል-11<br>ፋይናንሻል-9<br>ቴክንክና ፋይናንሻል-5 | S/20/NCB/RP/GE/2008 EFY | አልተገኘም | ሰንጠረዥ 3 ላይ ተመላክቷል |

**ሠንጠረዥ 2፡ - የሁለተኛ ጨረታ ሂደት**

| ተ.ቁ | የፕሮጀክት ስም | ፕሮጀክቱ መገኛ | ርዝመት | የጨረታው አይነት | የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ስለማሲያዝ | ለሥራ ተቋራጭ ጨረታ የወጣበት ቀንና የጨረታ ቁጥር | ጨረታውን የገዙ ብዛት | ጨረታውን ሞልተው የመለሱ ብዛት | ጨረታው የተከፈተበት ቀን | ለቴክኒክና ፋይናንሻል ያለፉ ብዛት | አማካሪ ጨረታ የወጣበት ቀን እና የጨረታ ቁጥር | የአዋጭነት ጥናት ስለመካሄዱ | የወሰን ማስከበር ስራ አፈፃፀም (ከውል በፊት ስለመከናወኑ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አጣጥ ማዞሪያ - ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሌራ | ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | 96.95 ኪ.ሜ | ግልጽ | ኦሮሚያ ኢንሹራንስ ካምፓኒ 510,652,594.16 | እ.ኤ.አ ሰኔ 10 እና 11/2022 W/52/ICB/OC/GOE/2014 EFY | 9 | 3 | እ.ኤ.አ ነሐሴ 30/2022 | 1 | እ.ኤ.አ ነሐሴ 22/23/2020 በጨረታ ቁጥር S/28/NCB/RP/GOE/ 2013 EFY | ተካሂዷል | ብር 229,100,000 ክፍያ ተፈፀመ ሲሆን ቀሪ ብር 41,706,585.31 |
| 2. | ወራቤ-ቦጀበር | ማዕከላዊ ሪጅን (ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል) | 40.5 ኪ.ሜ | ግልጽ | አባይ ኢንሹራንስ 79,500.000 | እ.ኤ.አ ታህሳስ 21 & 22/2018 W/21/NCB/OC/GOE/2011 EFY | **6** | **5** | እ.ኤ.አ ጥር 9/2019 | ቴክንክና ፋይናንሻል-2 | S/15/NCB/RFP/GOE/2011EFY | አልተካሄደም | **ሰንጠረዥ 3 ላይ** |

**ሠንጠረዥ 3፡ - የሦስተኛ ጨረታ ሂደት**

| ተ.ቁ | የፕሮጀክት ስም | ፕሮጀክቱ መገኛ | ርዝመት | የጨረታው አይነት | የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ስለማሲያዝ | ለሥራ ተቋራጭ ጨረታ የወጣበት ቀንና የጨረታ ቁጥር | ጨረታውን የገዙ ብዛት | ጨረታውን ሞልተው የመለሱ ብዛት | ጨረታው የተከፈተበት ቀን | ለቴክኒክና ፋይናንሻል ያለፉ ብዛት | አማካሪ ጨረታ የወጣበት ቀን እና የጨረታ ቁጥር | የአዋጭነት ጥናት ስለመካሄዱ | የወሰን ማስከበር ስራ አፈፃፀም (ከውል በፊት ስለመከናወኑ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ወራቤ-ቦጀበር | ማዕከላዊ ሪጅን (ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል) | 38.5 ኪ..ሜ | ቀጥታ | አባይ ኢንሹራንስ 277,725, 294.04 | የጨረታ ቁጥርW/45/NCB/DA/GOE /2015 EFY | በቀጥታ ግዥ የተካሄደ | | | | እ.ኤ.አ ጥቅምት 07/2024፣ የጨረታ ቁጥር ERA-NCB-C-0035-2015 BID | አልተካሄደም | ብር 123,848,000 ክፍያ ተፈፀመ ሲሆን ቀሪ ብር 188,094,000.04 |

## አባሪ 2

**ሠንጠረዥ 1፡ - የመጀመሪያ የውል አስተዳደር**

| ተ.ቁ | የፕሮጀክት ስም | የስራ ተቋራጩ ስም | ከስራ ተቋራጩ ጋር ውል የተዋዋሉበት ቀን | ለመስራት የሚፈጀው ጊዜ | የመጀመሪያው በጀት | የአማካሪው ስም | ከአማካሪው ጋር ውል የተዋዋሉበት ቀን | የአማካሪው ክፍያ መጠን | በውሉ መሰረት እስካሁን የደረሰበት ፊዚካል አፈፃፀም | በውሉ መሰረት እስካሁን የደረሰበት ፋይናንሽያል አፈፃፀም | ተጨማሪ የተፈቀደ በጀት (ካለ) | የሚጠናቀቅ ጊዜ | ውሉ የተቋረጠበት ጊዜ | ውሉ የተቋረጠበት ምክንያት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አጣጥ ማዞሪያ -ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሌራ | ሻንዶግ ሃይ ዌይ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን | እ.ኤ.አ ሚያዚያ 23/2017 | 42 ወራት | 1,165,299,596.00 | ዋይት ናይት ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኮንሳልታንት ኃ.የተ.የግ.ማ | እ.ኤ.አ መስከረም 13/2017 | 20,670,100.00 | ERA 25.96; ECA 31.93 | ERA 31.90%; ECA 31.93% | የለም | እ.ኤ.አ የካቲት 7, 2022 | እ.ኤ.አ 20/11/2020 | በፕሮጀክት አስተዳደር እና በሳይት ሀብት ቅንጅት ደካማ አፈጻጸም መኖር፣ አግባብ ያልሆነ የገንዘብ ፍሰት መኖር፣ የማቴሪያል ግምገማ በወቅቱ አለማድረግ ተጠቃሽ ናቸው |
| 2 | ወራቤ-ቦጀበር | የማነ ግርማይ ጀነራል ኮንትራክተር | እ.ኤ.አግ ንቦት 20/2016 | 1095 ተጨማሪ 90 ቀን | 458,445,650,00 | ሲቪል ዎርክስ አማካሪ መሀንዲስ | እ.ኤ.አ ጥር 6/2017 | 19,965,211.85 | 21.77% | 19.37% | የለም | ጥር 23 ቀን 2018 | እ.ኤ.አ ጥር 25/ 2018 | Ref.No As1/17/20.66 01/03/2018 እ.ኤ.አ በተጻፈ ደብዳቤ ለሥራ ተቋራጩ የ14 ቀን ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ በውሉ መሠረት ያለውን ሥራ ተቋራጩን አቋርጦ ከጣቢያው ሊያባርረው ይችላል፣ ጥር 23 ቀን 2018 ተቋርጧል፤ 1. የወሰን ማስከበር ክፍያዎች መዘግየት<br>2. የተራዘመ የዘናብ ጊዜ<br>3. ጠጠር ማምረት መዘግየ |

**ሠንጠረዥ 2፡ - የሁለተኛ የውል አስተዳደር**

| ተ.ቁ | የፕሮጀክት ስም | 2ኛ ስራ ተቋራጭ ስም | ከ2ኛ ስራ ተቋራጭ ጋር ውል የተዋዋሉበት ቀን | ለመስራት የሚፈጀው ጊዜ | የሁለተኛው በጀት ብር | 2ኛ አማካሪው ስም | ከአማካሪው ጋር ውል የተዋዋሉበት ቀን | የአማካሪው የክፍያ መጠን | በውሉ መሰረት እስካሁን የደረሰበት ፊዚካል አፈፃፀም | በውሉ መሰረት እስካሁን የደረሰበት ፋይናንሽያል አፈፃፀም | ከ2ኛው ውል ተጨማሪ የተፈቀደ በጀት (ካለ) | 2ኛው ውል የሚጠናቀቅ ጊዜ | 2ኛው ውል የተቋረጠበት ጊዜ | ውሉ የተቋረጠበትምክንያት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አጣጥ ማዞሪያ - ጉንችሬ -ኮሴ- ጌጃ- ሌራ | አለማየሁ ከተማ አጠቃላይ ኮንትራክተር | እ.ኤ.አ ህዳር 16/2022 | 38 ወራት | 5,106,525,941.61 | አይዲኮን ኢንፍራስትራክቸር ዴቨሎፕምተ ኮንሳልቲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ | እ.ኤ.አ ሰኔ 15/2021 | 21,552,782.50 | ERA 16.22 ECA 16.75 | ERA 16.22%; ECA 16.75% | የለም | እ.ኤ.አ ጥር 10/2026 | በስራ ላይ ያለ | በስራ ላይ ያለ |
| 2. | ወራቤ- ቦጀበር | ማርካን ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ | እ.ኤ.አሐምሌ 22 ቀን 2019 | 36 ወራት +1 ዓመት | 795,000,000.00 | እስታዲአ ኢንጂነርንግ ዎርክስ ኮንሰልታንት ፒኤልሲ | እ.ኤ.አ 10/2019 | 18,451,520.00 | ERA 16.84 % (ECA 40.78 %) | ERA 40.77% (ECA 40.70%) | የለም | አልተገኘም | መጋቢት 2023 | Ref.No As1/69/22.236 01/03/2023 እ.ኤ.አ ሥራው የተቋረጠው ከማርካን ትሬዲንግ የአሠሪው ተወካይ በኤስ.ኤ.ዲ/ደብሊው/ቢ/058/22 ዲሴምበር 16 ቀን 2022 ለማስተካከል የ30 ቀናት ማስታወቂያ ወጥቶ ስላልሰራ የተቋረጠ፡፡ በአሠሪው የተወከለው የውክልና ጊዜ ያለፈበት፣ ምንም ማሻሻያ ያልተደረገበት፣ ያላቸውን ዝግጅት ከግምት ውስጥ በማስገባት ቀሪ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ ስላልቻሉ፣ ሥራውን በፍጥነት ባለማከናወን፣ ሥራውን በቸልታ ማየት፣ |

**ሠንጠረዥ 3፡- የሦስተኛ የውል አስተዳደር**

| ተ.ቁ | የፕሮጀክት ስም | የ3ኛ ስራ ተቋራጭ ስም | ከ3ኛ ስራ ተቋራጭ ጋር ውል የተዋዋሉበት ቀን | ለመስራት የሚፈጀው ጊዜ | የሦስተኛው በጀት ብር | 3ኛ አማካሪው ስም | ከአማካሪው ጋር ውል የተዋዋሉበት ቀን | የአማካሪው የክፍያ መጠን | በውሉ መሰረት እስካሁን የደረሰበት ፊዚካል አፈፃፀም | በውሉ መሰረት እስካሁን የደረሰበት ፋይናንሽያል አፈፃፀም | ከ3ኛው ውል ተጨማሪ የተፈቀደ በጀት (ካለ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ወራቤ-ቦጀበር | አማራ መንገድ ሥራዎች ኢንተርፕራይዝ | እ.ኤ.አ መስከረም 7/2023 | 24 ወራት + 3 ወራት | 2,777,25 2,940.30 | ኤስ .ጂ ኮንስልታንሲ ኢንጂነሪግ ፒ.ኤል.ሲ | እ.ኤ.አ ጥቅምት 07/2024 በኤሌክትሮኒክስ ግዥ የተፈፀመ | 12,401, 743.75 | ERA 21.77% ወይም ECA 22.66% | ERA 19.37% ወይም ECA 22.66% | የለም |

**ሠንጠረዥ 4፡ - የመጀመሪያው የተጀመሩበት ጊዜ፣ መጠናቀቅ የነበረባቸው ጊዜ፣ የተቋረጡበት ጊዜ እና የተቋረጡበትን ምክንያት የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ፕሮጀክቱ ባለቤት | ፕሮጀክቱ ስም | ፕሮጀክቱ ስራ ተቋራጭ | ፕሮጀክቱ የተጀመረበት ጊዜ | ፕሮጀክቱ መጠናቀቅ የነበረበት ጊዜ | ፕሮጀክቱ የተቋረጠበት ጊዜ | ፕሮጀክቱ የተቋረጠበት ምክንያት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር | 1. አጣጥ ማዞሪያ - ጉንችሬ - ኮሴ - ጌጃ - ሌራ | ሻንዶግ ሃይ ዌይ ኢንጂነሪንግ | እ.ኤ.አ ግንቦት 23/2017 | እ.ኤ.አ ሐምሌ 20/11/2020 | እ.ኤ.አ ህዳር 20/2020 | ስራ ተቋራጩ ለፕሮጀክቱ ግንባታ የሚያስፈለጉ ቁሳቁሶች ማቅረብ ባለመቻሉ እና በፕሮጀክቱ ሳይት ላይ ምንም አይነት የስራ እንቅስቃሰ ባለመኖሩ (የስራ ተቋራጩ ደካማ አፈፃፀም) |
| | 2. ወራቤ-ቦጀበር | የማነ ግርማይ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ | እ.ኤ.አ ግንቦት 20/2016 | እ.ኤ.አ ጥር 25 ቀን 2020 | እ.ኤ.አ መጋቢት 01 ቀን 2018 | ስራ ስራ ተቋራጩ ለፕሮጀክቱ ግንባታ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች እና ማሽነሪዎች በውሉ መሰረት ባለማቅረቡና ባለመጠቀሙ (የስራ ተቋራጩ ደካማ አፈፃፀም) |

**ሠንጠረዥ 2፡ - የሁለተኛው የተጀመሩበት ጊዜ፣ የመጠናቀቅ ጊዜ/የነበረባቸው ጊዜ፣ የተቋረጡበት ጊዜ እና የተቋረጡበትን ምክንያት የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ፕሮጀክቱ ባለቤት | ፕሮጀክቱ ስም | ፕሮጀክቱ ስራ ተቋራጭ | ፕሮጀክቱ የተጀመረበት ጊዜ | ፕሮጀክቱ መጠናቀቅ ጊዜ/ የነበረበት ጊዜ | ፕሮጀክቱ የተቋረጠበት ጊዜ | ፕሮጀክቱ የተቋረጠበት ምክንያት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር | 1. አጣጥ ማዞሪያ - ጉንችሬ - ኮሴ - ጌጃ - ሴራ | አለማየሁ ከተማ ጀነራል ኮንትራክተር | እ.ኤ.አ ህዳር 16/2022 | እ.ኤ.አ 2025 (በ38 ወራት) | እየተሰራ ይገኛል | እየተሠራ ይገኛል |
| | 2. ወራቤ-ቦጀበር | ማርካን ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማህ | እ.ኤ.አ ሐምሌ 22 ቀን 2019 | 36 ወራት + ከ90 ቀናት | እ.ኤ.አ ታህሳስ 16 ቀን 2022 | ስራ ስራ ተቋራጩ ለፕሮጀክቱ ግንባታ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች እና ማሽነሪዎች በውሉ መሰረት ባለማቅረቡና ባለማጠቀሙ (የስራ ተቋራጩ ደካማ አፈፃፀም) |

**ሠንጠረዥ 3፡- የሥስኛው የተጀመረበትና የሚጠናቀቅበት ጊዜ**

| ፕሮጀክቱ ባለቤት | ፕሮጀክቱ ስም | ፕሮጀክቱ ስራ ተቋራጭ | ፕሮጀክቱ የተጀመረበት ጊዜ | ፕሮጀክቱ መጠናቀቅ ጊዜ | ፕሮጀክቱ የተቋረጠበት ጊዜ | ፕሮጀክቱ የተቋረጠበት ምክንያት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር | 3. ወራቤ-ቦጀበር | የአማራ መንገድ ሥራዎች | እ.ኤ.አ መስከረም 07/2023 | ፕሮጀክቱን በ24 ወራት+90 ቀናት | እየተሰራ ይገኛል | እየተሠራ ይገኛል |

## ዋቢ ማጣቀሻዎች

### 1. ሕጎች

- የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ደንብ ቁጥር 247/2003 ዓ.ም
- የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 ዓ.ም
- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ዓ.ም
- የፌዴራል መንግሥት ግዥ አፈፃፀም መመሪያ 2002 ዓ.ም
- ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ደንብ ቁጥር 524/2015 ዓ.ም
- የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረሙስና አዋጅ ቁጥር 1236/2013 ዓ.ም

### 2. ጥናቶች

- Construction Works of Atat Mazoria - Gunchire - Kose-Geja - Lera Road Porject W/44/ICB/OC/GOE/2009 EFY & W/52/ICB/OC/GOE/2014 EFY
- Construction Works of Worabe - Bojaber Road Porject W/33/NCB/OC/GOE/2007 EFY, W/21/NCB/OC/GOE/2011 EFY & W/45/NCB/DA/ GOE/2015 EFY
- Consultancy Service for Continuation of Construction Atat Mazoria-Gunchire-Kose-Geja-Lera Road Porject S/73/NCB/RP/GOE/2009/EFY & S/28/NCB/RP/ GOE/2013 EFY
- Consultancy Service for Continuation of Construction Worabe - Bojaber Road Porject፡ S/20/NCB/RP/GE/2008 EFY, S/15/NCB/RFP/GOE/2011EFY & ERA-NCB-C-0035-2015 BID.
- Transparency International's "Curbing Corruption in Public Procurement, A Practical Guide, 2014

### 3. ቃለ መጠይቆች

ይህ ቃለ መጠይቅ በከተማና መሠረተ ልማት ዘርፍ (በከተማና መሠረተ ልማት ሚ/ር፣ በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደርና በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን) ለአመራሮችና ሠራተኞች፣ በመንገድ ፕሮጀክቶች አካባቢ ለሚገኙ የአካባቢ ነዋሪዎች እና የአካባቢው መስተዳደር አካላት የተዘጋጀ ነው፡፡

**የቃለ-መጠይቁ ዓላማ፡-**

የመንገድ ፕሮጀክቶች የጨረታ ግዥና የውል አስተዳደር ግልፅነትና ተጠያቂነት ሁኔታ፣ ሙስናና ብልሹ አሠራር የሚያመላክቱ ድርጊቶች፣ የሚያስከትለው ጉዳትና የችግሩ መንስዔ ምን እንደሆነ በመለየት የመፍትሄ ምክረ ሀሳብ ማቅረብ ነው፡፡

የሚሰጡት ምላሾች ሚስጥራዊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚሰጡት መረጃ ለጥናት አገልግሎት ብቻ በማዋል በቀጣይ የመንገድ ፕሮጀክቶች የጨረታ ግዥና የውል አስተዳደር ከሙስናና ብልሹ አሠራር እና ድርጊት በፀዳ ሁኔታ ተፈጻሚ እንዲሆን በማድረግ ከኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ዘርፍ የሚጠበቀውን ያህል ጥራትና መጠን በጠበቀ መልኩ በመሥራት የተጀመረውን የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ማስቀጠል የሚያስችል አቅጣጫ ለመቀየስ ወሳኝነት ያለው መሆኑን በመገንዘብ ትክክለኛ ምላሽ እንዲሰጡን በአክብሮት እየጠየቅን ውድ ጊዜዎን መስዕዋት በማድረግ ምላሽ በመስጠት ስለተባበሩን በቅድሚያ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

1. **የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር** በደንብ ቁጥር 247/2003 ዓ.ም ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር

1.1 አንቀጽ 7(7) የሥራና የአማካሪነት ውሎችን ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ይዋዋላል፣ ሥራዎችን በየውላቸው መሠረት የሚከናወኑ መሆናቸውን በበላይነት ይቆጣጠራል ወይም በሌላ አካል ቁጥጥር እንዲካሄድ ያደርጋል፤

1.1.1 የሥራ ተቋራጭና የአማካሪነት የጨረታ ግዥና የውል ዝግጅት ከግልጽነት አንፃር ምን ይመስላል?

1.1.2 የሥራ ተቋራጭና የአማካሪ ውሎችን እንዲዘጋጁ ያደርጋል ስለሚል በእነማን ይዘጋጃል?

1.1.3 በውላቸው መሠረት ማከናወናቸውን የሚደረገው ቁጥጥር ምን ይመስላል?

1.1.4 በአፈጻጸም መጓደል በታዩ ክፍተቶች በተቋራጭ ላይ የሚወሰድ እርምጃ ምን ይመስላል?

1.1.5 በሌላ አካል ቁጥጥር ይካሄዳል ወይ? በነማን?

1.2 አንቀጽ 7(9) የመንገድ ሥራዎች በአገር ውስጥ ወይም በዓለም አቀፍ ጨረታ የሚከናወኑበትን አማራጭ ይወስናል ስለሚል፤

1.2.1 የተወሰኑ አማራጮች ካሉ ቢራራ፣

1.3 የመንገድ ፕሮጀክቶች ዝቅተኛ አፈፃፀም ሲያሳዩ፣ ለረጅም ጊዜ ሲዘገዩ እና ውሉ ሊጠናቀቅ 3 ወር እስኪቀረው ድረስ ለምን ወቅታዊ ቁጥጥር አልተደረገም? ለምን አስቀድሞ ማስቆም አልተቻለም?

1.4 በናሙና በታዩ 2 የመንገድ ፕሮጀክቶች በተደጋጋሚ ውል በመቋረጡ መንግስት ለከፍተኛ ወጪ ተዳርጓል፤ ይህን ለማስቀረት ለምን ወቅታዊ ክትትል አልተደረገም?

1.5 የመንገድ ፕሮጀክቶች በሚፈለገው ደረጃ ሳይከናወኑ ሲቀር ፈጣን ውሳኔ ለምን አይሰጥም? በተለይም በተደጋጋሚ እየተቋረጡ ለሚቀጥሉና መንግስትን ለከፍተኛ ወጪ የዳረጉ መንገዶች ላይ ወጪውን ለማስቀረትና መፍትሄ ለመስጠት የተደረገ ጥረት ምንድን ነው?

**2. የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 ዓ.ም ለከተማና መሠረተ ልማት ሚንስቴር ከተሰጠ ሥልጣንና ተግባር ውስጥ፡-**

2.1 አንቀጽ 31(1)ሐ) የመንገድ ፕሮጀክቶች ሥራ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታነትንና ፍትሐዊ ተደራሽነትን መሠረት ባደረገ መልኩ መከናወናቸውን ይከታተላል ስለሚል፣

2.1.1 በዕቅድ መሰረት የተሰሩ/ያልተሰሩ ሥራዎች በትክክል ስለመከናወናቸው (ስለመፈፀማቸው) በምን መንገድ ትከታተላላችሁ?

2.2 አንቀጽ 31 (1)ከ) በዲዛይን፣ በጨረታና፣ በኮንትራት ይዘት ላይ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ የሚል ንዑስ አንቀጽ አለ፣

2.2.1 የመንገድ ፕሮጀክቶችን በሚመለከት የተዘረጋው የተጠያቂነት ሥርዓት ምን ይመስላል?

2.2.2 አፈፃፀሙን የተከታተላችሁበት መንገድ ምንድን ነው?

2.2.3 የመንገድ ፕሮጀክቶች የሚያጋጥማቸው ችግሮችን ለመፍታት የተደረገ ድጋፍ ካለ፣

2.2.4 በተለይም በተደጋጋሚ እየተቋረጡ ለሚቀጥሉና መንግስትን ለከፍተኛ ተጨማሪ ወጪ የዳረጉ መንገዶች ላይ የተወሰደ እርምጃ ካለ ቢገለጽ፣

**3. ለኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን በደንብ ቁጥር 524/2015 ዓ.ም በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር፡-**

3.1 አንቀጽ 7(3) መሰረት በዲዛይን፣ በጨረታ፣ በኮንትራት ይዘትና በውል አስተዳደር እንዲሁም በግንባታ ጥራት እና ቁጥጥር ግልፅና ተጠያቂነት ያለው የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤ ስለሚል፡-

3.1.1 የመንገድ ፕሮጀክቶች በዲዛይን፣ በጨረታ፣ በኮንትራት ይዘትና በውል አስተዳደር እንዲሁም በግንባታ ጥራት እና ቁጥጥር ግልፅና ተጠያቂነት ያለው ሥርዓት ዘርግታችኋል ወይ?

3.1.2 በተሰጣችሁ ሥልጣንና ተግባር የተከታተላችሁ ከሆነ የተከታተላችሁት አፈፃፀም ምን ይመስላል?

3.1.3 ያረጋገጣችሁበት መንገድ ምንድነው? ቁጥጥሩ እንዴት ተከናወነ?

3.2 በአንቀጽ 7(5) ለመሰረተ ልማት ሥራዎች ግንባታ ሞዴል፣ ስፔስፊኬሽን፣ የልኬት ሥርዓትና ማንዋል ያዘጋጃል፤ ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤ ከሚለው አንፃር፡-

3.2.1 ለመንገድ ፕሮጀክት ግንባታ የተዘጋጁ ሞዴሎች፣ ስፔስፊኬሽን፣ የልኬት ሥርዓትና ማንዋል ካሉ ቢገለጽ፤

3.2.2 ያረጋገጣችሁበት መንገድ ምንድነው? ቁጥጥሩ ምን ይመስላል?

3.3 በአንቀጽ 7(6) በጨረታና ውል መሰረት  በዲዛይን፣ በዋጋ፣ በጥራትና በጊዜ ተሰርተው ስለመጠናቀቃቸው እና ርክክብ ስለመደረጉ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል የእርምት እርምጃ ይወስዳል ስለሚል፤

3.3.1 በጨረታና ውል መሰረት በዲዛይን፣ በዋጋ፣ በጥራትና በጊዜ ተሰርተው ስለመጠናቀቃቸው እና ርክክብ ስለመደረጉ የተደረገ ክትትልና ቁጥጥር ምን ይመስላል?

3.3.2 የተወሰደ የእርምት እርምጃ ካለ ቢገለጽ?

3.4 በአንቀጽ 7(10) የግንባታ ሞዴል ዋጋዎች እና የግምት መስሪያ ቀመሮች ያዘጋጃል፤ የዋጋ ግምቶች በአግባቡ ስለመዘጋጀታቸው ይቆጣጠራል፤ ያረጋግጣል ይላል፤

3.4.1 የመንገድ ፕሮጀክት የግንባታ ሞዴል ዋጋዎች እና የግምት መስሪያ ቀመሮች ተዘጋጅተዋል?

3.4.2 የዋጋ ግምቶች በአግባቡ ስለመዘጋጀታቸው ቁጥጥሩና ማረጋገጡ ምን ይመስላል?

3.5 በአንቀጽ 7(12) መሥራት ለሚችሉ ሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና በዘርፉ የሚሳተፉ ሌሎች ድርጅቶችን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፣ ያግዳል፣ ያሳግዳል፣ ይሰርዛል፣ ወይም ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤ስለሚል፣

3.5.1 ለመንገድ ፕሮጀክት ሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጣችኋል? ምን ያህል?

3.5.2 የታገዱ፣ የተሰረዙና ህጋዊ እርምጃ የተወሰደባቸው ካሉ ቢገለጽ?

## <u>የፌደራል ስነምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን የሙስና መከላከል ጥናት</u>

## <u>በመንገድ ፕሮጀክት ጥናት ለመስክ ምልከታ የተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ (Check lists)</u>

### 1. <u>ለቡታጅራ አካባቢ ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በየደረጃው ላሉ አመራሮች የውል አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት መሰረት ያደረገ ጥያቄ፤</u>

1. የመንገድ ፕሮጀክት ስራው እንዴት እና ለምን ተመረጠ? የአዋጭነት ጥናት ተጠንቷል ወይ? የጥናት ውጤቱ ምን ይመስላል?
2. የመንገድ ፕሮጀክቱ መቼ ተጀመረ? የመስክ (ሳይት) መሐንዲስ በቋሚነት አለ ወይ?
3. የአፈር ጥናት ተደርጓል ወይ? መቼ? አዋጪነቱስ? በአግባቡ ባለመጠናቱ ያመጣው ችግር አለ ወይ? ምንድነው?
4. ፕሮጀክቱ በስምምነቱ መሰረት የቤተ ሙከራ (የጥራት መለኪያ ላቮራቶሪ) ተገንብቷል? የተሟላ ነው? የሥነ ልክ ፍተሻ ተደርጓል? በጊዜው ምርመራ እንዲደረግ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርገው ማን ነው? የምርመራ ውጤቱ ተዓማኒነት ምን ይመስላል?_
5. የሰው ኃይልና የማሽነሪ ቁጥጥር ምን ይመስላል?
6. የግብዓት (ማቴሪያል) አቀርቦት በሚፈለገው ደረጃ ነው? ነዳጅ፣ ሲሚንቶና ሌሎች ግብዓቶች ማን ያቀርባል? አቅርቦቱ ምን ይመስላል?
7. የአፈር ሥራ፣ ሰብቤዝና ድሬኔጅ ሥራዎች ምን ደረጃ ላይ ይገኛሉ?
8. የወሰን ማስከበር ቦታዎች የትኞቹ ናቸው? የካሳ ክፍያ ተጠናቋል? ካልተጠናቀቀ እስካሁን ለምን አልተጠናቀቀም?

9. ማሽነሪ በሥራ ተቋራጭ ወይስ በአሰሪ ተቋሙ ወይስ በክራይ የቀረበ ነው?

10. የገቡ ማሽኖች (ማቴሪያሎች) እንዳይወጡ ምን ዓይነት ቁጥጥር ይደረጋል?

11. የሥራ ተቋራጭ ሥራውን ሲቋርጥ ያስገባው ዕቃ በመያዣነት ይያዛል? ያስገባው ዕቃ ምን ነበር? አሁንስ አሉ ወይ? ካሉ ግምታቸው ምን ያህል ነው?

12. ሳይት ቡክ (ሰነዶች) ምን ይመስላሉ? ማየት ቢቻል፣

13. ከመጀመሪያው ውል ውጪ የፍላጎት፣ የኪ.ሜ. ለውጥ ተደርጓል ወይ? ከተደረገ ለምን? ምን ያህል? ለ2ኛውና 3ኛው ሥራ ተቋራጭ ምን ያህል ለውጥ ተደርጓል?

14. የግንባታ የግብዓት ማምረቻ ሳይቶች (ቢሮ ሳይቶች፣ የፓይፕ ፕሮዳክሽን፣ ቤዝ ኮርስ ፕሮዳክሽን (ክሬሸር ሳይት)፣ ወዘተ. ተሟልተዋል ወይ?

15. የፕሮጀክቱ የፊዚካልና ፋይናሽያል ዓመታዊ እቅድ ስንት ነው? አሁን ያለው አፈፃፀም ስንት ነው? የየካቲት፣ የመጋቢትና ሚያዝያ 2017 ዓ.ም መርሃ ግብር (Action plan) ሪፖርት ምን ይመስላል? በሰነድ ቢቀርብ፣

16. ሥራ ተቋራጮች ፕሮጀክቱን በተደጋጋሚ በማቋረጣቸው መንግስት ለከፍተኛ ተጨማሪ ወጪ ተዳርጓል፤ ለመጀመሪያው ሥራ ተቋራጭና አማካሪ ምን ያህል ወጪ ወጥቷል? ለሁለተኛው ሥራ ተቋራጭና አማካሪ ምን ያህል ወጪ ወጥቷል? እንዲሁም ለሦስተኛው ሥራ ተቋራጭና አማካሪ ምን ያህል ወጪ ወጥቷል?

17. በተደጋጋሚ ሥራው ሲቋረጥ ምን ምን ችግሮች ነበሩ? በተከሰተው ችግር ምን ብልሹ አሠራር ነበር?

18. የአካባቢ የመስተዳድር አካላት የፕሮጀክቱን አፈፃፀም ለመከታተልና ለመደገፍ ያላቸው ቁርጠኝነት ምን ይመስላል?

19. የአካባቢ ነዋሪዎች ስለፕሮጀክቱ ያላችው ግንዛቤ ምን ያህል ነው?

## 2. ለመንገድ ሥራ ተቋራጭ የቀረበ ጥያቄ፣

1. በውሉ ውስጥ የተዘረዘሩትን ውሎችና እና ሁኔታዎች በተስማሙበት የጊዜ ሰሌዳ እና በጀት ፕሮጀክቶች ይጠናቀቃሉ? ካልተጠናቀቁ ለምን?
2. የፕሮጀክት ፋይናንስን በኃላፊነት እያስተዳደሩ ለንዑስ ተቋራጮች እና አቅራቢዎች በወቅቱ ይከፍላሉ? የክፍያ ሰነድ ካለ፣
3. ፕሮጀክቱን ያገኙት በምን ዓይነት የጨረታ ግዢ ነው?
4. ይህ ፕሮጀክት በመኖሩ ያገኙት አገልግሎት ወይም ጥቅም ምንድን ነው?
5. የመንገድ ፕሮጀክቱ ከሙስናና ብልሹ አሰራር ያለውን ተጋላጭነት ምን ይመስላል?
6. ስለፕሮጀክቱ የአካባቢ አስተዳድር አካላት ያላቸው ግንዛቤ እና የፕሮጀክቱን አፈፃፀም ለመከታተልና ለመደገፍ ያላቸው ቁርጠኝነት ምን ያህል ነው?

## 3. ለመንገድ ፕሮጀክቱ አማካሪ ድርጅት የቀረበ ጥያቄ፣

1. ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት የዋጭነት፣ የወጪ ግምት እና የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ከተቋሙ ጋር ተወያይተዋል?
2. በውሉ ውስጥ የተዘረዘሩትን ውሎችና የህግ መስፈርቶች ስለመከበራቸው ሥራው ከመጀመሩ በፊት ውሎችን የመገምገም ሥራ ተሰርቷል? ካልተሰራ ለምን?
3. ለፕሮጀክት የሚፈለጉ መስፈርቶች የሥራ ተቋራጩ አሟልቶ ገብቷል ብለው ያምናሉ? ካላሟሉ በእርሶ በኩል ምን የተወሰደ እርምጃ አለ? ቢጠቅሱ፣
4. ፕሮጀክቱን ያገኙት በምን ዓይነት የጨረታ ግዥ ዓይነት ነው?
5. ይህ ፕሮጀክት በመኖሩ ያገኙት አገልግሎት ወይም ጥቅም ምንድነው?
6. የመንገድ ፕሮጀክቱ ከሙስናና ብልሹ አሰራር ያለውን ተጋላጭነት ምን ይመስላል?
7. ስለፕሮጀክቱ ሂደት ለውጦች ሲኖሩና ስጋቶች ሲኖሩ ለደንበኞች፣ ለተቋራጮች እና ሌሎች ባለድርሻ አካለት መካከል ውይይት ያደርጋሉ? ካለ በዝርዝር ቢያስረዱን፣ ቃለ ጉበኤ ቢያሳዩን፣
8. የመንገድ ፕሮጀክቱ ላይ አለመግባባቶችን እና በሙያዊ እና በውሉ መሰረት የተፈቱ ችግሮች አሉ? ካሉ በዝርዝር ቢያስረዱን፣

## 4. <u>የአካባቢ ነዋሪዎች የቀረበ ጥያቄ፣</u>

1. <u>የመንገድ ፕሮጀክቱ እንዲሰራ</u> ያወያያችሁ አካል አለ ወይ? ጊዜውንና ሁኔታውን ካስታወሱ ቢያብራሩልን?
2. የመንገድ ፕሮጀክቱ የተጀመረበት መቼ ነው? ምን ያህል ጊዜ ፈጀ?
3. <u>የመንገድ ፕሮጀክቱ ለህብረተሰቡ ያለው ፋይዳ ወይም አስፈላጊነት</u> ምንድነው?
4. የመንገድ ፕሮጀክቱ በማነው የሚሰራው የሚያውቁት ከሆነ ያወቁበት መንገድ በምንድን ነው?
5. በመንገዱ መሰራት ምን ያህል ተጠቃሚ ያረጋችኋል? በዝርዝር ቢገለጽ፣
6. ይህ ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ የሚያገኙት አገልግሎት ወይም ጥቅም ምንድነው?
7. የመንገድ ፕሮጀክቱ ሲሰራ የነበረው ብልሹ አሰራር ምን ይመስላል?
8. ሙስናና ብልሹ አሰራር ወይም ቅሬታ ለመቀበል የሚያስችል ሥርዓት አለ ወይ?
9. ስለፕሮጀክቱ የአካባቢ መስተዳድር አካላት ያላችው ግንዛቤ እና የፕሮጀክቱን አፈፃፀም ለመከታተልና ለመደገፍ ያላቸው ቁርጠኝነት ምን ይመስላል?
10. <u>የመንገድ ፕሮጀክቱ ለማጠናቀቅ ለምን ረጅም ጊዜ ፈጀ? ምክንያቱ ምንድነው?</u>
11. የመንገድ ፕሮጀክቱ መጀመሩ በህብረሰበቡ ዘንድ ያመጣው ለውጥ ምንድነው? የተገኙ ለውጦች ዝርዝር ቢያብራሩልን፤

## 5. <u>ለአካባቢ አተስተዳደር አካላት የቀረበ ጥያቄ፣</u>

1. የመንገድ ፕሮጀክት ለማሰራት ምን ያህል የሥራ ተቋራጭ እና አማካሪዎች ተሳትፈዋል?
2. የመንገድ ፕሮጀክቱ አጠቃላይ በጀት ምን ያህል እንደሆነ ይታወቃል?

3. የመንገድ ፕሮጀክቱ የተጀመረበት ጊዜ መቼ ነው?
4. የመንገድ ፕሮጀክት የሚጠናቀቅበትን ጊዜ ታውቃላችሁ?
5. የመንገድ ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት ከህብረተሰቡ (ከሚመለከተው አካል) ጋር ውይይት ተደርጓል? (ስለጠቀሜታው፣ ስለበጀቱ፣ወዘተ.) ሰነድ አባሪ ኮፒ ይደረግ፣
6. የመንገድ ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት መንገዱ የሚነካቸው የህብረተሰብ አካላት ካሣ ተከፍሏል ወይ ? ያልተከፈለ ካሣ ካለ? መረጃ ኮፒ አባሪ ይደረግ፤
7. የመንገድ በፕሮጀክቱ የሚቀርቡ አገልግሎቶች በሚገባ ለህብረተሰቡ ምን ያህል ተደራሽ/ተጠቃሚ ተደርጓል?
8. የመንገድ ፕሮጅክቱ በህብረሰበቡ ላይ የሚያመጣው ለውጥ ምንድነው?
9. የመንገድ ፕሮጀክቱ የዕቅድ፣ ክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማ እና አፈፃፀም ሂደት ምን ይመስላል?
10. የመንገድ ፕሮጀክቱን አስመልክቶ የቀረቡ ጥቆማዎች ካሉ በዝርዝር ይቅረብ? መረጃ አባሪ ኮፒ ይደረግ፣
11. የመንገድ ፕሮጀክቱን የሚከታተል ተወካይ (Focal person) ተመድቧል? የምደባ ኮፒ አባሪ፣ ካልተመደበ ያልተመደበበት ምክንያት ምንድነው?

## 6. ለሁሉም ተጠያቂዎች የሚቀርብ ጥያቄ፣

1. ፕሮጀክቱ ከተያዘለት በጀት፣ ጊዜ፣ እና ሕብረተሰቡ መስጠት ካለበት አገልግሎት አንፃር እንዴት ይመለከቱታል?
2. የፕሮጀክቱ እንቅስቃሴ ግልፅነትን ተላብሶ ከመከናወን አኳያ ያሎት ኃሳብ ምንድን ነው?